# አጥቢያን የማስፋት መርህ

# መግቢያ፡-

## ራዕይ የመሰነቅ ሰርቶማሳያ (ዎርክሾፕ)

ለሰርቶማሳያው አስተባባሪ የተዘጋጀ መምሪያ

### መግለጫ

ይህ ሰርቶ ማሳያ መሪዎች ጤናማ ቤተክርስቲያንን የመትከል ብቃት እና አስፈላጊነት ላይ ጥልቅ ምልከታ እና ገለጻ እንዲያደርጉ ያግዛል፡፡ በዚህ ክፍል የሚከተሉት ርዕሶች ይዳሰሳሉ፡- የቤተክርስቲያን ተከላ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሰረቶች፣ ቤተክርስቲያን ተከላ ላይ የተሰማሩ አገልጋዮች እና ቤተሰቦቻቸው ማንነት መግለጫ፣ ቤተክርስቲያንን የመትከል እርምጃ፣ ቤተክርስቲያንን የመትከል ሞዴል እና የጤናማ ቤተክርስቲያን ባህሪያት ናቸው፡፡

መልቲፕሊኬሽን ኔትዎርክ
ብዙ አጥቢያ ያላት፤ ጠንካራ ቤተክርስቲያን

**የአሰልጣኙ መምሪያ**

አጥቢያ የማስፋ መርህ መግቢያ ሰርቶ ማሳያ ከ11 የአሜሪካ አህጉር አገራት በተወጣጡ 22 ሰዎች በተጻፈ *Sembremos Iglesias Saludables* በተሰኘ እና በ Dr. John Wagenveld አዲተርነት የተዘጋጀ እና በ FLET and UNILIT አታሚዎች በላቲን ቋንቋ ታትሞ በቀረበ መጽሐፍ አሳብ ላይ መሰረት አድርጎ የተጀመረ ነው፡፡ ይህ መጽሐፍ በመጀመሪያ ይገኝ የነበረው በስፓኒሽ ቋንቋ ብቻ ነበር፡፡ በ2007 ዓ.ም ለመጀመሪያ ጊዜ *Planting Healthy Churches* በሚል ርዕስ በዘጠኝ ጸሐፊያን ተደርሶ በDr. Gary Teja እና Dr. John Wagenveld ተዘጋጅቶ ቀረበ፡፡ ይህ ሰርቶ ማሳያ የቀድሞ ስሙ ጤናማ ቤተክርስቲያን መትከል ነበር፡፡

በዚህ ማኑዋል አሳብን ለማንጸባረቅ የሚረዱ ጥያቄዎች እና ተግባራት ተካትተውበታል፡፡ እነዚህ ጥያቄዎች እና ተግባራት በግልም ሆነ በቡድን ሊተገበሩ የሚችሉ ናቸው፡፡ ከእነዚህ ተግባራት እና ጥያቄዎች ውስጥ አሁን ለመስጠት ላሰብከው ሰርቶ ማሳያ ስልጠና ይሆናሉ የምትላቸውም ጥያቄዎች በመምረጥ ከተጠቀምክ በኋላ፤ ተሳታፊዎች በቀጣይ ለጥናት ይጠቀሙበት ዘንድ ሌሎችን ጥያቄዎች ለግል ጥናት ይወስዱ ዘንድ አበረታታ፡፡

ይህን ሰርቶ ማሳያ ስልጠና በመስጠቱ ረገድ እርደታ ትፈልግ እንደሆን፤ በአካባቢህ ከሚገኙ የመልቲፕሊኬሽን ኔትዎርክ ሚኒስትሪስ አስተባባሪዎች አንዱን ለማግኘት ሞክር፡፡ የእነዚህ አስተባባሪዎች አድራሻ በድረ ገጻችን ላይ ይገኛል፡፡

ለስርቶ ማሳያው ስልጠና አስተባባሪዎች የቀረቡ አጋዥ ግብአቶች፡-

1. የአሰልጣኙ ማኑዋል

2. የተሳታፊዎች ማኑዋል

3. ተንቀሳቃሽ ጽሑፎች (PowerPoint slides) በሲዲ ወይንም በሶፍት ኮፒ በድረ ገጻችን ላይ ቀርበዋል፡፡

4. ከመልቲፕሊኬሽን ኔትዎርክ ሚኒስትሪስ አሰልጣኞች እርዳታ ማግኘት (አድራሻቸውን ለማግኘት ድረ ገጻችንን ጎብኝ)፡፡

መልቲፕሊኬሽን ኔትዎርክ ሚኒስትሪስ መጋቢዎችን እና መሪዎችን በማሰልጠን የቤተክርስቲን ተከላን እድገት ያፋጥናል፡፡ በwww.multiplicationnetwork.org ድረገጽ የማሰልጠኛ እና መሰልጠኛ ማዋሎችን ታገኙ ዘንድ ሁኔታውን ያመቻቸን ሲሆን በጥራዝ ለማግኘት ለምትፈልጉም ታትመው የተዘጋጁ ማኑዋሎችን ማግኘት ትችላላችሁ፡፡

**ይህን መምሪያ እንዴት መጠቀም እንደሚቻል የቀረበ ጥቆማ**

ይህ የአሰልጣኙ መምሪያ በተሳታፊዎች ማኑዋል ውስጥ የቀረቡትን መረጃዎች እና ለቀረቡ ጥያቄዎችም የሚሆኑ መልሶችን አካትቶ የቀረበ ነው፡፡ ከዋናው ጽሑፍ በስተግራ ባለው ሰፋ ያለ ህዳግ ለአሰልጣኙ ብቻ የቀረቡ ተጨማሪ ብራሪያች ይገኛሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በዋናው ጽሑፍ ውስጥ **የአሰልጣኙ መምሪያ** በሚል ርዕስ ተግባራቱን እንዴት መምራት እንደሚቻል የሚያስረዳ መረጃ ይዟል፡፡ አንድ ልብ ልንለው የሚገባ ጉዳ ቢኖር፤ እያንዳንዱ አሰልጣኝ ልምዱን፣ የአገላለጥና ምሳሌ አቀራረብ ምርጫው እንዲሁም ጊዜው እንደሚፈቀደው ይህን ማኑዋል ለማሻሻል ሙሉ ፈቃድ እንዳለው ነው፡፡ ምክንያቱም በዚህ ማኑዋል የቀረቡትን አሳቦች በሙሉ ለማቅረብ እና ለመወያየት የሚሆን በቂ ጊዜ በስልጠናው ሂደት ስለማይገኝ፡፡ በመሆኑም በዚህ ማኑዋል ውስጥ በጣም አስፈላጊ የሚባሉትን በስልጠና ወቅት ከተገበርካቸው በኋላ የተቀሩትን ተሳታፊዎች በቤታቸው እንዲያጠናቅቁ ማሳሰብ አስፈላጊ ነው፡፡

**የሚመከር የጊዜ አጠቃቀም**

እኛ ለአንድ ቀን ይሆናል ብለን ያሰብነውን የአንድ ቀን የጊዜ በጀት እንዴት መጠቀም እንደሚቻል ምክራችንን ሰጥተናል፤ እናንተ ደግሞ ለሰልጣኞቻችሁ እና ላላችሁበት ሁኔታ ይመጥናል የምትሉትን የጊዜ አጠቃቀም ማሰናዳት ትችላላችሁ፡፡ እንዳስፈላጊነቱ አንዱን ክፍለትምህርት በአንድ ሳምንት በመጠቀም በአንድ ወር ውስት መጠቅለል ይቻላል፤ ካስፈለገ ደግሞ አርብ ምሽት እና ቅዳሜ ጠዋትን በመጠቀም ወጪን ለመቀነስ እና ስልጠናውን ማጠናቀቅ ይቻላል፡፡

እያንዳንዱ ክፍለትምህርት በአንድሰዓት ተኩል ጊዜ ውስጥ እንዲሰት ተደርጎ ተዘጋጅቷል፡፡ ይሁን እንጂ በስተመጨረሻ ተሳታፊዎች የግምገማውን ቅጽ የሚሞሉበትን በቂ ጊዜ መስጠታችሁን ልብ በሉ፡፡

የሚቻል ከሆነ የስልጠናውን ሂደት በዲጂታል ምስል መቅጫ ካሜራ ፎቶግራፎችን ማንሳት እና ለኤም ኤን ኤም በmultiplicationNetwork@gmail.com. ኢሜይል አድራሻ መላክ ይቻላል፤ ይህን በበለጠ ለመረዳት በዚህ ማኑዋል ላይ የቀረበውን ሪፖርት ያድረጊያ ቅጽ መመልከት ይቻላል፡፡

የስልጠናው ግብአቶች

ግባችን ይህ የሰርቶ ማሳያ ስልጠና አቅማችን በፈቀደ መጠን እጅግ በርካታ ለሆኑ መሪዎች በአነስተኛ ወይንም ምንም ሳይከፍሉ የሚያገኙበትን መንገድ ማመቻቸት ነው፡፡ እንደውም እናንተ የአሰልጣኙን መምሪያ ኮፒ በምታደርጉበት ዋጋ እንድታገኙ ወይንም ኮፒ በማድረግ፤ ቤተክርስቲያናት በስልጠናው ወቅት የሚያስፈልገውን የሻይ ጊዜ ወጪ ብቻ በመሸፈን ስልጠናውን ማግኘት ይቻላል፡፡

ይህን ማኑዋል ለምትጠቀምበት ማህበረሰብ አውድ ይሆናል ብለህ የምታስበው የሽፋን ዲዛይን መንደፍ እና መጠቀም ይቻላል፡፡

መልቲፕሊኬሽን ኔትዎርክ ኔትዎርክ

በተለየ መልኩ ካልተገለጠ በቀር ሁሉም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ተወሰዱት ከ1954ቱ ትርጉም ነው፡፡

## ማውጫ


ክፍል 1 | ጤናማ ቤተክርስቲያን መትከል ለምን አስፈለገ..............................4

ክፍል 2 | ማነው ቤተክርስቲያን መትከል ያለበት......................................13

ክፍል 3 | ማቋቋም የምንፈልገው ቤተክርስቲያን ምን መምሰል አለበት.....27

ክፍል 4 | ቤተክርስቲያን ለመትከል ምን አይነት እርምጃ መውሰድ ያስፈልገናል..43

**ስርተፊኬት**..........................58


| ስልጠናውን ለመስጠት የሚመከር የጊዜ ሰንጠረዥ | |
|---|---|
| ምዝገባ እና እንኳን ደህና መጣችሁ | |
| የአምልኮ እና ጸሎት ጊዜ | 30 ደቂቃ |
| ክፍል 1 | 90 ደቂቃ |
| ክፍል 2 | 90 ደቂቃ |
| ረፍት | |
| ክፍል 3 | 90 ደቂቃ |
| ክፍል 4 | 90 ደቂቃ |
| የጥያቄ እና መልስ፣ ግምገማ እና መዝጊያ ክፍለጊዜ | |

ሁሉም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የተወሰዱት በ1954 ከታተመው አማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ነው፡፡

# ክፍል 1

## ጤናማ ቤተክርስቲያን መትከል ለምን አስፈለገ?

*“ብዙ ልዩ ልዩ የእግዚአብሔር ጥበብ አሁን በቤተ ክርስቲያን በኩል በሰማያዊ ስፍራ ውስጥ ላሉት አለቆችና ሥልጣናት ትታወቅ ዘንድ”* ኤፌ 3፡10

ይህን ስእላዊ መግለጫ ከተሳታፊዎች መጽሐፍ በመጠቀም በክፍለትምህርት ı ላይ የቀረቡትን አራቱም መሰረቶች ማስረዳት ይቻላል፡፡

### ዓላማ

የዚህ ክፍለ ትምህርት ዓላማ አዳዲስ ቤተክርስቲያናትን የመትከል መጽሐፍ ቅዱሳዊ፣ ስነመለኮታዊ፣ ሚሲዮናዊ እና ስልታዊ መሰረቶች ማሳየት ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አዲስ አማኝ ማህበረሰብን በመፍጠሩ ረገድ ያለውን ተቃውሞ ማሳየት እና ይህን ለመከወን ሊኬድባቸው የሚችለውን ሰፊ አማራጮች ያስቀምጣል፡፡

***መግቢያ* | *መሰረታዊያን***




**ትርጉም**

ጤናማ አብያተክርስቲያናትን መትከል በሚለው ክፍል ውስጥ ዶ/ር ቻርለስ ቫንኢንጌን የሚከተለውን መጽሐፍ ቅዱስን መሰረትያደረገ ቤተክርስቲያን ተከላ ቀመርን እደሚከተለው አቅርበዋል፡፡

*"ጤናማ ቤተክርስቲያናትን የመትከል ምንጭ እና ጠቃሚ የሆነው የፍቅር እና የርህራሄ አምላክ፤ ወንዶች እና ሴቶች የኢየሱስ ክርስቶስ ደቀመዝሙር እዲሆኑ ከዚህ በተጨማሪ ሃላፊነት የሚሰማቸው የቤተክርስቲያን አባላትና የክርስቶስ አካል እንዲሆኑ ራሱ ሰሉሱአሃድ የሆነው እግዚአብሔር ነው፡፡ እዚህ ሲሆን ምዕመናኑ ሁሉ ሊመጣ ላለው ለልዑል እግዚአብሔር እና ለእርሱ ክብር ምስክሮች ይሆናሉ፡፡"*

**ከላይ የተሰጠውን ትርጉም እደመነሻ በመጠቀም የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ**

በዚህ ትርጉም ምን አይነት የእግዚአብሔር ባህሪያት ተገልጸዋል?

1. <u>በፍቅር የተሞላ .</u>
2. <u>በምህረት የተሞላ .</u>

ከትርጉሙ በመነሳት እግዚአብሔር ምን የሚፈልግ ይመስላችኋል?

1. <u>የኢየሱስ ክርስቶስ ደቀመዛሙርት .</u>
2. <u>ኃላፊነት የሚሰማቸው የቤተክርስቲያን አባላት .</u>

የማህበረምዕመን መመስረት ምንን አመልካች ነው?

<u>ሊመጣ ያለውን የእግዚአብሔር መንግስት .</u>

ለምድን ነው ቤተክርስቲያን የምንተክለው?

<u>የእርሱ ክብር ይመሰገን ዘንድ .</u>

**የመክፈቻ ተግባር፡-** አዳዲስ ቤተክርስቲያናትን የምንተክልባቸው ምክንያቶች

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡-** ተሳታፊዎች ቤተክርስቲያን የሚተከልበት ምክንያት ብለው የሚያምኑበትን እንዲናገሩ እድል ስጥ፡፡ ከዚያም እነርሱ ያነሷቸው ምክንያቶች በዚህ ክፍለትምህርት ተጠቅሰው እንደሆን በጥሞና እንዲከታተሉ አሳስባቸው፡፡

**መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሰረት**

ጤናማ አብያተክርስቲያናትን ለመትከል የሚሆኑ አምስት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምክንያቶች አሉ

1. **ምክንያቱም እግዚአብሔር አብ የጠፉትን የሚፈልግ እና የሚያገኝ አምላክ ስለሆነ፡፡**
   ቁልፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃዎች ዘፍ 3፡9፤ መዝ 23፤ ሉቃ 14፡15-24
2. **የክርስቶስ ፍቅር ግድ ስለሚለን**
   ቁልፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃዎች 2ቆሮ 5፡14-20፤ ማቴ 18፡20፤ ዮሐ 14፡23
3. **መንፈስ ቅዱስ ለህዝብ ሁሉ ይደርስ ዘንድ የተላከ በመሆኑ**
   ቁልፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃዎች ሐዋ 2፡9-11፤ 13፡2-5፤ 1፡8
4. **ምክንያቱም አጥቢያ ቤተክርስቲያናት የእግዚአብሔር መንግስት ቅርንጫፍ ስለሆኑ**
   ቁልፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃዎች 1ጴጥ 2፡5፣ 9-10፣12፤ ቆላ 1፡13-23፤ ሮሜ 12
5. **አዳዲስ ቤተክርስቲያናትን መትከል ለእግዚአብሔር ክብርን የሚያመጣ ምክንያት በመሆኑ**

## ስነመለኮታዊ መሰረቶች

*ስቱዋርት ሙሬይ የተባለ ሰው Laying Foundations በተሰኘ መጽሐፉ ስነመለኮታዊ መሰረቶችን ጠቅለል አድርጎ አቅርቦልናል፡፡ የቤተክርስቲያን እድገትም ሆነ አዳዲስ ቤተክርስቲያናትን መትከል ቢያንስ ሶስት መርሆ ይኖረዋል፡-*

1. **የክርስቶስ በስጋ መገለጥ (ትስጉት)**
   ልክ እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ በስጋ መገለጥ ራሱን ከሰው ጋር እንዳስተዋወቀ፤ ቤተክርስቲያንም እንዲሁ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ በማህበረሰቡ አምሳል እና ፍላጎት ተገልጣ የወንጌሉን ሙሉ መልዕክት ማድረስ ይገባታል፡፡ በአንድ አካባቢ ያለ ማህበረ ምዕመን ላለበት አካባቢ የክርስቶስ አካል ግልጠት ሲሆን በክርስቶስ ኢየሱስ ስለሚገኝ ሕይወት መልካሙን የምስራች ለማድረስ ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር ተመሳስላ ትገኛለች፡፡

   **ቁልፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃዎች**፤ ፊሊ 2፡5-8፤ ዮሐ 1፡1፣ 1፡14

   "በታሪክ ውስጥ ብዙ ሰዎች እንደ አማልክት የመሆን ፍላጎት የሚያድርባቸው ሲሆን፤ ነገርግን አንዱ እና ብቸኛው አምላክ (እግዚአብሔር) ሰው ሆነ"
   -ምንጭ የማይታወቅ

2. **የመለኮት ተልዕኮ**

የመጽሐፍ ቅዱሱ አምላክ እግዚአብሔር ያለማቋረጥ የጠፉትን ለማግኘት እና ድህነት እና ስርነቀል ለውጥ ያገኙ ዘንድ ፍለጋ ላይ ያለ አምላክ ነው፡፡ በተመሳሳይ ቤተክርስቲያንም እግዚአብሔር ሰዎችን ደቀመዝሙር የሚያደርግበትን ተግባር እና ስርአት በመከተል፣ ማህበረሰብን በመለወጥ እና እግዚአብሔርን ወክላ እና ከእግዚአብሔር ጋር ሆና እርሱ ለሚያመጣው ለውጥ ጠቃሚ መሳሪያ በመሆን አሁን በምድር ላይ እየተገለጠ ያለውን መገኘቱን እና ተግባሩን ማሳለጥ ይጠበቅባታል፡፡

**ቁልፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃዎች፤** ዮሐ 3፡16 ማቴ 28፡18-20፤ ማር 16፡15-16፤ ሉቃ 24፡46-49

*"እሳት ለመንደድ መቀጣጠል እንደሚያስፈልገው ሁሉ ቤተክርስቲያንም ህልውንዋ ተልዕኮ ነው"* - ኢሚል ብረነር

### 3. የእግዚአብሔር መንግስት

ቤተክርስቲያን የምታውጀው እና የምታመላክተው ኢየሱስ ያወጀውን እና ያመላከተውን ነው፤ እርሱም የእግዚአብሔር መንግስት መምጣት! ቤተክርስቲያን መልዕክት የምትሰጠው፣ የአንድ አካባቢን ማንነት የምትላበሰው (incarnates) እና የእግዚአብሔርን መልካምነት እንዲሁም በፈጠራቸው ፍጥረታት ላይ በጽድቅ የሚገዛ እንደሆነ በማመላከት ነው፡፡

**ቁልፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃዎች፤** 1ጴጥ 2፡9-12፤ ቆላ 1፡13

*"ነገር ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ፥ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል።"* ኢየሱስ ክርስቶስ - (ማቴ 6፡33)

## የተልዕኮ መሰረቶች

Craig Van Gelder የተባለ ጸሐፊ *Essence of the Church* በሚል ርዕስ በጻፈው መጽሐፍ ውስጥ ቤተክርስቲያን እና ተልዕኮዋን በተመለከተ ሶስት አስፈላጊ ነጥቦችን አመላክቷል፡፡

**ቤተክርስቲያን ነች፣ ቤተክርስቲያን የሆነችውን ትሰራለች እንዲሁም የምትሰራውን ታደራጃለች**

1. ቤተክርስቲያን ምንድን <u>ናት</u> (በባህሪ/በይዘት) በ1ጴጥ 2፡9-10፤ ኤፌ 4፡24፤ 1ቆሮ 12፡12-13

የእርሱ ሕዝብ ይሆኑ ዘንድ እግዚአብሔር የፈጠረው ማህበረሰብ፣ ለህብረተሰብ እና ለተፈጥሮ የለውጥ መሳሪያ የሆነች ቤተክርስቲያን ናት፡፡

ቤተክርስቲያን በእውነተኛ ጽድቅ እና ቅድስና እግዚአብሔርን ለመምሰል በክርስቶስ ኢየሱስ የተፈጠረው አዲሱ ሰው ናት፡፡ ቤተክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ ወደ አንድ ቤተሰብነት የተካተተ የክርስቶስ አካል ናት፡፡

1. ቤተክርስቲያን ምንድን ናት

የቤተክርስቲያን ምንነት እና ባህርይ ከእግዚአብሔር የመጣ እና በእርሱ የሚወሰን ነው፡፡ ቤተክርስቲያን በእግዚአብሔር ተፈጥራ ለሰዎች ጥቅም የተሰጠች ናት፡፡ በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር የሰጠን ስጦታ (በጸጋ የተፈጠረው ማህበረሰብ) እንደ ቤተክርስቲያን የምንኖርበት ምክንያት ነው፡፡ የዚህ ሁለንተናዊ ግዳጅ አንዱ መገለጫ ደግሞ የቤተክርስቲያን ተከላ ነው፡፡

2. ቤተክርስቲያ ምን እየሰራች ነው

የቤተክርስቲያን ባህርይ ስራዋን ይወስናል፤ እነርሱም፡- ማስታወቅ፣ ማወጅ፣ ግልጋሎት እና አገልግሎት ናቸው፡፡ ቤተክርስቲያን የሚባለው የእግዚአብሔር ህዝብ ተልዕኮውን ይዞ መንቀሳቀሱን ነው፡፡ ቤተክርስቲያን የምትሰራው የሆነችውን ነው፡፡ ልክ ውሻ በተፈጥሮው እንደሚጮህ ሁሉ ቤተክርስቲያንም ሰዎች ህብረትን በመፍጠር "እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃኑ የጠራችሁን የእርሱን በጎነት እንድትናገሩ የተመረጠ ትውልድ፥ የንጉሥ ካህናት፥ ቅዱስ ሕዝብ፥ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ" (1ጴጥ 2፡9)

2. ቤተክርስቲያን ምንድን **ትሰራለች** (በተግባር/ዓላማ) 1ጴጥ 2፡9-10፣ 12

ቤተክርስቲያን የምትከውነው ማንኛውም ተግባር ቤተክርስቲያን የሆነችውን መሰረት በማድረግ ነው፡፡ ቤተክርስቲያን በክርስቶስ ኢየሱስ፣ ወንጌልን በተለየ አውድ በመቅረጽ እና በመለኮት ተልዕኮ ውስጥ አብሮ ሰራተኛ በመሆን የተገለጠውን የእግዚአብሔርን መንግስት ትሰብካለች/ታውጃለች፡፡ የክርስቲያን መቀደስ ከተቀመጠለት ወንጌሉን የማወጅ፣ ሌሎችን የመጥቀምና አገልጋይነት ተግባር ጋር ተያይዞ የሚከናወን ነው፡፡ ቤተክርስቲያን የምትሰራው የሆነችውን ነው፡፡ ልክ ውሻ የሚጮኸው በተፈጥሮው እንደዚያ ለመጮኽ የተሰራ እደሆነ ሁሉ፤ ቤተክርስቲያንም ተልዕኮዋን(ሌሎች በወንጌል የመድረስ ስራ) የምታከናውነው እንደዚሁ ተፈጥሮዋ ስለሆነ ነው፡፡

3. ቤተክርስቲያኒቱ የምትሰራውን **ታደራጃለች** (በቅርጽ/አደረጃጀት)

በመጨረሻም ቤተክርስቲያኒቱ ካለችበት አውድ እና ልትጠቀምበት በምትችል ስልት ራሷን አደራጅታለች ስርአትም አበጅታለች፡፡ ቤተክርስቲያኒቱ የተጠራችበትን ጥሪ ለመከወን፤ ለስራዋ ሊታወቅ የሚችል ቅርጽ መስጠት ያስፈልጋታል፡፡ ቤተክርስቲያን ተፈጥሮዋን እና ዓላማዋን በትክክል ከተገነዘበች፤ ራስዋን በጥሪዋ ልክ ራስዋን ቅርጽ እድታሲዝ እና እንድታደራጅ የሚያስችላት ቁልፍ ይህ ብቻ ነው፡፡

3. ቤተክርስቲያን የምታደረጀው የምትሰራውን ነው

ቤተክርስቲያን ባህርይዋን እና ዓላማዋን ስትረዳ፤ አደረጃጀቷን የተሰጣትን ተልዕኮ ዙሪያ የሚያጠነጥን ይሆን ዘንድ ታመቻቻለች፡፡ የጠፉትን መድረስ ከቤተክርስቲያን አገልግሎቶች አንደ አንድ ተጨማሪ አገልግሎት የምንይዘው ሳይሆን የቤተክርስትያን ተፈጥሮ ግብአት ነው፡፡ ቤተክርስቲያን የህልውናዋን መገለጥ የምታዘጋጀው የጠፉትን በወንጌል መድረስ ዙሪያ ነው፡፡

## ተግባራዊ መሰረቶች

ዳንኤል ሳንቼዝ *Planting Healthy Churches* በተሰኘ መጽሐፉ የመጀመሪያ ምዕራፍ ቤተክርስቲያን የምንተክልበትን ስልታዊ አመክንዮዎችና ቤተክርስቲያን በመትከል ሂደት ውስጥ የተለመዱ እንቅፋቶች/ ተቃርኖዎችን ዳስሷል፡፡ ከዚህ በታች ጠቅለል ተደርገው ተዘርዝረውልናል፡፡

1. <u>የህዝብ ብዛት</u> በፍጥነት በማደግ ላይ ይገኛል፡፡
2. አዳዲስ ቤተክርስቲያናት ከተመሰረቱ ከቆዩ ቤተክርስቲያናት <u>በበለጠ</u> ህዘቦችን በወንጌል ይደርሳሉ፡፡
3. ቆየት ያሉ ቤተክርስቲያናት <u>ያሉበትን ሁኔታ ጠብቆ ወደማቆየት</u> ያደላሉ፡፡
4. አዳዲስ ቤተክርስቲያናት <u>ነባር</u> ቤተክርስቲያናትን በማነቃቃት ያግዟቸዋል፡፡
5. ቤተክርስቲያናት በጣም የሚፈለጉት ያልዳኑ ሰዎች <u>በሚኖሩበት</u> አካባቢ ነው፡፡
6. አዳዲስ ቤተክርስቲያናት በበለጠ <u>ለመቃኘት የተመቹ (flexible) ናቸው</u>
7. አንድ ቤተክርስቲያን ብቻዋን <u>ህዝብን ሁሉ</u> ለመድረስ አትችልም፡፡
8. አዳዲስ ቤተክርስቲያናት <u>መሪዎችን</u> በቶሎ ያሳድጋሉ/ያዘጋጃሉ፡፡
9. <u>መቀራረብ</u> ደቀመዝሙርነትን ያግዛል፡፡

**አሳባችሁን ግለጹ:-**

እስከአሁን አስበሃቸው የማታውቃቸው ቤተክርስቲያን የመትከል ምክንያቶች የትኞቹ ናቸው? የትኞቹስ ምክንያቶች በአካባቢህ ከአንተ ጋር እየሰሩ ያሉ ሰዎችን ቤተክርስቲያን እንዲተክሉ ያነሳሳቸዋል?

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

## የተለመዱ እንቅፋቶች/ተቃርኖዎች

***የአሰልጣኙ መምሪያ:-*** *ተሳታፊዎች ከዚህ በፊት እነርሱ ያሰቡት ወይንም ሌሎች ሰዎች የነገሯቸው ተቃርኖዎች ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ውስጥ ከተመለከቱ በስተግራ በቀረቡት ምልክት ማድረጊያ ሳጥኖች ውስጥ ምልክት እንዲያደርጉ ተይቃቸው::*

1. አዳዲስ ቤተክርስቲያናት ሲበዙ ቆየት ያሉ ቤተክርስቲያናትን ያዳክማሉ::
2. አዳዲስ ቤተክርስቲያናትን ማቋቋም ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቅ ነው::
3. ብዙ አባሎቻችንን እናጣለን::
4. እኛ አሁን ከበቂ በላይ ያልተሟሉ ፍላጎቶች አሉን::
5. የቤተክርስቲያን ተከላን በግድ እንዲከናወን ማድረግ አንችልም::
6. የቤተክርስቲያናችንን አስተምህሮ መጠበቅ እንዳንችል ያደርገናል::
7. አዳዲስ ቤተክርስቲያናትን መትከል በአጥቢያዎች መካከል ፉክክር እንዲፈጠር ያደርጋል::
8. አንድ ቤተክርስቲያን ለአንድ ከተማ የአዲስ ኪዳን አስተምህሮ ነው::
9. አዲስ ቤተክርስቲያናትን መጀመር ስራዬን በአግባቡ እንዳልከውን ያደርገኛል::

**አስተያየታችሁን ግለጹ:**

ከዚህ ከመጀመሪያው ክፍለትምህርት የትኛውን አሳሳቢ እንቅፋት/ተቃርኖ እንድትገነዘቡ እና ምላሽ እንድትሰጡ ረዳችሁ?

______________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

## ቤተክርስቲያን የመትከል ራዕይ፡-

ለምንድን ነው አዳዲስ ቤተክርስቲያናትን መክፈት በጣም አስፈላጊ የሆነው? ስቱአርት ሙሬይ እንዲህ በማለት በጥሩ ሁኔታ ጠቅለል አድረጎ አቅርቦታል፡-

*የቤተክርስቲያን እድገትም ሆነ የአዳዲስ ቤተክርስቲያናት መተከል በራሱ ግብ አይደለም፡፤ ሁለቱም ለስነመለኮታዊው የእግዚአብሔርን መንግስት የማስፋት መርህ ደጋፊ ናቸው፡፡ ቤተክርስቲያን መትከል በአብዛኛው የእግዚአብሔር*

> *መንግስት ትርጉም ባለው መንገድ ያስፋፋል፤ በአዳዲስ ሰፍራዎችና አዳዲስ መንገዶች የመንግስቱን የሕይወት ዘይቤ በአካል ገልጠው የሚያሳዩ አማኝ ማህበረሰብን መመስረት፤ ሁለንተናዊ የሆነን ወንጌል መስበክ፤ ላሉበት ማህበረሰብ ጨው እና ብርሃን መሆን፤ ላሉበት አውድ ትንቢታዊ እይታን ማምጣት የሚችሉ፤ ኢፍትሃዊነትን ፊት ለፊት የሚጋፈጡ፣ ለድሆች እና ለተጠቁ ጥብቅና መቆምና ድምጽ ማሰማት፤ የተሰበረን ሕይወት ለመጠገን ከሌሎች ጋር ተቀናጅቶ መስራት፤ እዲሁም በህዝብ እና በማህበረሰብ ፈውስ ሂደት ውስጥ ተባባሪ መሆን፡፡ እንዲህ ያሉ ቤተክርስቲያናት መትከል የእግዚአብሔር መንግስት ምልክት ነው፡፡*
>
> - ከቤተክርስቲያን ተከላ *መሰረት ማኖር* ከሚለው ክፍል በጥቂቱ ተስተካክሎ የቀረበ

ቤተክርስቲያን ተከላ የእግዚአብሔርን መንግስት ለማስፋት ዘርን እንደመዝራት ስለሆነ በእጅጉ አስፈላጊ ነው፡፡ ግባችን የእግዚአብሔር መንግስት ነው፡፡ ቤተክርስቲያን ተከላ በተቀናጀ መንገድ የእግዚአብሔርን መንግስት የማስፋት አካል ነው፡፡ እግዚአብሔር ቀድሞ በዚህ ተግባር ውስጥ ተግባሩን በማከናወን ላይ የሚገኝ ሲሆን፤ እኛም ከእርሱ ጋር እንድንሰራ ተጋብዘናል! ሙሬይ የተባለው ጸሐፊ ይህን ግንዛቤ እንድንወስድ አጽንኦት ሰጥቶበታል፤ “ቤተክርስቲያኔን እተክላለሁ” ይሁን እንጂ ለጴጥሮስ የ “የመንግስቱን ቁልፍ” ሰጥቶታል (86)፡፡ ክርስቶስ ሕይወትን የሚለውጥ በስጋ የተገለጠ ቃል ነው፤ በመሆኑም የእርሱ የሆነን እንድንሄድና ሰዎችን ደቀመዝሙር በማድረግ አዳዲስ አማኝ ማህበረሰብን ለመሰብሰብ ተሹመናል፡፡ እግዚአብሔር ለመንግስቱ ከያዘው ጉዳይ ውስጥ አንዱ ቤተክርስቲያን ተከላ ነው፡፡ በዚህ ሁሉ ውስጥ ኢየሱስ የእግዚአብሔር መንግስት ዘሪም ዘርም ነው፡፡

የእግዚአብሔር የልብ አሳብ በሺዎች የሚቆጠሩ ጤናማ ቤተክርስቲያናት በአህጉራቸሁ እንዲተከሉ ነው! ይህን እውን ለማድረግ በአንድም ሆነ በሌላ ትሳተፋለህ/ትሳተፊያለሽ?

# ማስታወሻ

# ክፍለትምህርት 2

# ማነው ቤተክርስቲያን መትከል ያለበት?

በዚህ ክፍል የቀረበውን ስዕላዊ መግለጫ እንደመግቢያ ልትጠቀምበት ትችላለህ፡ ፡

ላማቅረብ የተፈለገው አሳብ፤ አንዳንድ ጊዜ ምንም እንኳን ሰዎች ለሚፈለጉበት የስራ ዘርፍ በቂ ዕውቀት እና ልምድ ባይኖራቸውም ጊዜ ስላላቸው ብቻ እንቀበላቸዋለን፡፡

## ዓላማ

የዚህ ክፍለትምህርት ዓላማ ውጤታማ የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋይ ሊኖ ዝርዝር ማሳየት ነው፡፡ በዚህም የቤተክርስቲያን ተከላ አገልግሎት ጥሪ አስፈላጊነ እንድምታውን ጎላ አድርገን ወይንም ትኩረት ሰጥተን እንመለከታለን፤ የሙ የተግባር ልምምድ ዝግጅት ሚና ይተነተናል፤ በተጨማሪም በቤተክርስቲያን ተ አገልጋይ ራሱን የሚገመግምበት መሳሪየም ይቀርባል፡፡

## መግቢያ




**የተግባር ልምምድ፡-** የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋዮች ባህሪያት

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡-** ተሳታፊዎች ሶስት ወይንም አራት ሰው በአንድ ቡድን በመሆን የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋዮች የግድ ሊኖራቸው ስለሚገባ ባህርያት ዝርዝር እንዲጽፉ እድል ስጥ፡፡ ከዚያም ተሳታፊዎች የዘረዘሯቸውን ባህርያት በዚህ ክፍለትምህርት ከተዘረዘሩት ጋር አመሳክር፡፡

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

# ሁለቱ ተቃራኒ ጫብጦች




አንዳንዶች የሚከተሉትን መልሶች እንደሆኑ ከግንዛቤ አስገብተዋል፡-


ሀ. **የሙሉጊዜ ትምህርት** | ለመበልጸግ ጠንክሮ የሚሰራው ሰው

የተሳሳተ መረጃ ከሙሉጊዜ ስልጠና እጦት ጋር ሲዳበል ሰዎች የከፋ ስህተት ወደመፈጸም

ያደርሳል፡፡

ለ. **የሙሉጊዜ ጥናት ጉድለት** | ሂዱና እነእከሌ “እንደሰሩት” የሰሩትን ያንኑ ደግማችሁ “ስሩት”

ከሴሚናሪዎች እና ከመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጆች የሙሉጊዜ ስልጠና በወሰዱና በተመረቁ ሰዎች ላይ ብቻ እምነታችንን ከጣልን፤ በፍጹም መላውን ማህበረሰብ መድረስ አንችልም፡፡ (የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ምሩቅ የሆኑ እና አለምን መድረስ የሚችሉ ሰዎች በበቂ ቁጥር ማግኘት አንችልም!)




ራሱን ባለጸጋ ለማድረግ ጠንክሮ ይሰራ የነበረ ግለሰብ ማስታወሻ፡- አንድ ደሃ ሰው አንድን ባለጸጋ እንዴት ይህን ሁሉ ገንዘብ እንዳካበተ ሲጠይቀው፤ ጠንክሮ በመስራቱ እንደሆነ ይነግረዋል፡ ፡ ከዚያም ደሃው ሰው አካፋውን እና ዶማውን ይዞ ወደ እርሻው በመሄድ ጠንክሮ ይቆፍር ጀመር፡፡ ይህ ሰው በቁፋሮው ከፍ ያለ ጥረትን ለወራት ቢያደርግም ምንም ጠብ ያለ ገንዘብ አልነበረም፡፡

**ሂዱና ልክ ጆ "እንደሚሰራው" እናንተም ስሩ፡፡** ይህን ማስታወሻ የጻፈው ግለሰብ የአንድ ድርጅት አስተዳደር ሲሆን፤ የጻፈበት ምክንያትም ሁሌም ስለ ደንበኛ አያያዝ ስለሚያጠኑ ነገር ግን አንድም እቃ መሸጥ ለማይችሉ ሁለት ግለሰቦች ምን ያህል ተስፋ እደቆረጠባቸው ለማሳየት ነው፡ ፡ ምንም እንኳን ጆ በትምህርቱ ብዙ ያልገፋ እና ጓደኞቹ የሚቀልዱበት ቢሆንም ማንኛውንም እቃ ለየትኛውም ግለሰብ የመሸጥ ብቃት ነበረው፡፡

የጠቋሚ መስመሮቹ ተቃርኖ እና ልዩነት የሚገጥመንን ተግዳሮት ያሳየናል፡፡

## ቤተክርስቲያን ተከላ ላይ ለማሰማራት ማንን እናዘጋጃለን እንዴትስ ግለሰቡን ለአገልሎቱ የተዘጋጀ እንዲሆን እናደርጋለን?

**መ. ብዥታውን እንዴት ማጥራት ይቻላል?** የስራ መሳሪያውን ስሎ የተነሳ ሰው ጠንከሮ፣ ብስለት በተሞላበት ሁኔታ ሊሰራ ይገባዋል፡፡

- መከ 10፡10
- ሐዋ 18፡24-28
- እንዴት ነው የሙሉ ጊዜ ስልጠና የሚረዳህ?

  ________________________________________.

  ________________________________________.
- “በስራ” ላይ የተማርከው አንድ ነገር ምንድን ነው?

  ________________________________________.

  ________________________________________.

**ሞጁላር የትምህርት ስልትን በቤተክርስቲያን ተከላ ላይ ለተሰማሩ አገልጋዮች ማቅረብ**

ከአንድ ቀን ስልጠና እስከ አራት አመት የሴሚናር ዲግሪ ያለ ክህሎትን መሰረት ያደረገ የመስክ ስራን መሰረት ያደረገ ስልጠና ሞጁላር የትምህር ስልት ይባላል፡፡

**በቤተክርስቲያን ተከላ ላይ የሚሰማራውን አገልጋይ መምረጥ**

በቤተክርስቲያን ተከላ ስራ ላይ አቅም ኖሮት ሊሰማራ የሚችልን አገልጋይ የመለየት እና እውቅና የመስጠት ስራ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እና መንፈሳዊ ይዘቶች በተመራጩ ላይ ሊገኙ ይገባል፡፡

ሀ. **አንዱ አስፈላጊ መርህ** ▎ በዚህ አገልግሎት ላይ የሚሰማራው ግለሰብ በቅድሚያ በእግዚአብሔር የተጠራ ሊሆን ይገባል፡፡

*“በርናባስንና ሳውልን ለጠራኋቸው ሥራ ለዩልኝ አለ።”* ሐዋ 13፡1

ጄምስ ዲ. ክሬን *El Sermón Efcaz (Effective Preaching)* በተሰኘ በጽሐፉ ዓለምን ለማገልገል እየሰሩ ያሉ ሰዎች በእግዚአብሔር የመጠራትን አስፈላጊነት አስረግጦ ይነግረናል፡፡ ጳውሎስ በመጽሐፍ ቅዱስ ለመጠራት የሚያበቁ መስፈርቶችን የሚያረጋግጡ ሁለት ቃላትን ያስታውሰናል፡፡ (2ቆሮ 5፡18-20 እና 1ቆሮ 4፡1-2)፡

- **ሰጪ (Oikonos)** ▎ ያልተቀበላችሁትን መስጠት አትችሉም

በሌላ ጎን ደግሞ በአንድ ፋብሪካ ውስጥ የሽንኮራ አገዳ በመቁረጥ የሚተዳደር አንድ ግለሰብ ከጓደኞቹ ይልቅ ቶሎ ቶሎ ለእረፍት ስለሚቀመጥ አንድ ገለሰብ ታሪክ እናገኛለን፡፡ ይህ ግለሰብ ሌሎች ያለሚቋረጥ ሲቆርጡ እርሱ ቶሎ ቶሎ ለእረፍት ይቀመጥ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ከሁም የበለጠ የሚቆርጠው እርሱ ነበር፡፡ ታዲያ አንዳ የስራ ባልደረባው እንዴት ነው አንተ ሁሌም ከእኛ በበለጠ ታርፋለህ ግን ደግሞ ከእኛ የበለጠ ትቆርጣለህ፤ ሚስጥሩ ምንድን ነው ብሎ ቢጠይቀው፤ እንዲህ ነበር ያብራራው፡- እኔ ሁሌም ስቀመጥ ላርፍ ሳይሆን መቁረጫዬን ለመሳል ነው፤ ሌሎች የጊዜ ብክነት የሚመስላቸው እረፍት ይህን ሰው ውጤታማ አድርጎታል፡፡

የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋዩ ኃላፊነት የሚወስድባቸው ስፍራዎች፡- Ed Stetzer, የተባለ ጸሐፊ *Planting New Churches in a Postmodern Age* በተሰኘ መጽሐፉ የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋዩ እውን በሆነው ወይንም በአሳብ ብቻ ባልቆመው ቤተክርስቲያን ውስጥ ያለውን ኃላፊነት ግልጥ ለማድረግ ሞክሯል፡፡ ይህ ጸሐፊ የቤተክርስቲያን ተከላ አገልግሎት እጅግ አድካሚ እንደሆነ ሲያብራራ፤ አገልጋዩ በሳምንት ውስጥ ቢያንስ አስራ አምስት ሰዓታት ለወንጌል ስርጭት ሊመድብ ይገባል ይላል፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን አስር ሰዓታት ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና ለስብከት፣ ሌላ አስር ሰዓታት ያጠናውን ለማስጠናት እና አስራ አምስት ሰዓታት በመጋቢነት አገልግት ለሚያገለግላቸው መንጎች መስጠት ይጠበቅበታል፡፡ እየሰራ የሚያገለግል ከሆነ ደግሞ አምስት ሰዓታት ማለትም ሁለት ሰዓታት ለጥናት፣ ሁለት ሰዓታት ያጠናውን ለማስጠናት እንዲሁም ሶስት ሰዓታት በመጋቢነት የሚያገለግላቸውን ሰዎች ለመድረስ ሊጠቀምበት እንደሚገባ ጸሐፊው ያሳስባል፡፡ ከጸሐፊው ጋር ተስማማንም አልተስማማንም ለቤተሰብ መስጠት ያለብትን ጊዜ፣ ለግል የምንወስደውን የጥሞና ጊዜ እና ለሌሎች ኃላፊነቶች መስጠት ያለብትን ጊዜ ከግምት ውስጥ ሊያስገባ ግድ ነው፡፡ ይህን ስትመለከቱ የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋዩ ምን ያህል ራሱን የሚገዛ መሆን እንደሚገባው እና አገልግሎቱ ምን ያህል ጉልበት የሚጠይቅ እንደሆነ ማስተዋል ትችላላችሁ፡፡

- **እንደራሴ (Ambassador)** | የራሱን ሳይሆን የንጉሱን ፈቃድ የሚያስፈጽም

**ሰ. ከቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋይ ጋር ተያይዘው የሚነሱ አራት ነጥቦች** | አርቱሮ ሮብልስ የተባለ የMNM ባልደረባ የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋዮች የሚከተሉት የግድ ሊኖሯቸው ይገባል፡፡

1. **መለኮት**፤ ከ___እግዚአብሔር___
2. **እርግጠኝነት**፤ በራሱ እና በሌሎችሰዎች___
3. **በአንድ ጉዳይ ላይ ያተኮረ**፤ ለአንድ የተለየ___ማህበረሰብ /አገልግሎት
4. **ምልአት**፤ እግዚአብሔር የመራውን ስራ በመስራት የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋዩ ___እርካታን___ በአገልግሎቱ ያገኛል፡፡

## የውጤታም ቤተክርስቲያ ተከላ አገልጋይ ባህሪያት

ዶ/ር ቻርለስ ራይድሊይ በኢንዲያና ሁኒቨርሲቲpsychological counseling የዶክትሬት ዲግሪ አስተማሪ/ፕሮፌስር ሲሆን የአገልግሎት ምርጫን መመዘንን በልዩነት የሚያጠና እና በዚህም ዘርፍ እውቅናን ያተረፈ ግለሰብ ነው፡፡ ራይድሊይ ውጤታማ የሆነ የቤተክርስቲያ ተከላ አገልጋይን ባህሪያት ለመግለጽ አንድ መመዘኛ ቅጽ አዘጋጅቷል፡፡ የሚከተለው የተወሰደው የእርሱን ምርምር አጠር ባለ መልኩ በማስቀመጥ ነው፡፡

**ውጠታማ የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋይ...**

### 1. ባለራዕይ ናቸው

ውጤታማ የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋይ በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ለአገልግሎቱ የሚሆኑ መልካም አጋጣሚዎችን የመመልከት ብቃት ይኖረዋል፡፡ አገልጋዩ ወደፊት ሊሆን ያለውን ጥርት ባለ ሁኔታ ሙሉ ምስሉን መመልከት የሚችልና ከእርሱ ጋር ለሚያገለግሉ አጋሮቹ በትክክል ማስረዳት ይችላል፡፡ ጤናማ ቤተክርስቲያን የመትከል ራዕይ አገልጋዩ በአስቸጋሪ ሁኔታዎች እንኳን የማይናወጥ አቋም እዲኖረው ያደርጋል፡፡

ነህምያ ከእየሩሳሌም መፈራረስ ውስጥ አላማውን ሊያሳካ የሚችል አጋዥ እድል እንዳለ መመልከት ችሏል፡፡

“የአባቶቼ መቃብር ያለባት ከተማ ተፈትታለችና፥ በሮችዋም በእሳት ተቃጥለዋልና ፊቴ ስለ ምን አይዘን?” ነህ 2፡3

የዋልት ዲዝኒ ምሳሌ፡- አንዳንዶች እንዲህ ይላሉ ዲዝኒ የሚባለው የመዝናኛ ፓርክ አንዱ ክፍል እንደተጠናቀቀ ስራውን ሲመራ የነበረው መሃንዲስ ለዲዝኒ ሚስት፤ ባሏ ዲዝኒ ከጥቂት ጊዜ በፊት እንደሞተ ያረዳታል፤ ከተል አድርጎም "ዲዝኒ ይህንን ፓርክ ሳያይ ማለፉ ምን ያህል የሚያሳፍር ነው" አለ፡፡ ሚስቱም ለዚህ አባበሉ የመለሰችው እንዲህ ብላ ነበር "እኛ ከመስራታችን ብዙ ጊዜ በፊት እርሱ አይቶታል"

የዋልት ዲዝኒ ምሳሌ

### 2. የራስ ተነሳሽነት አላቸው

የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋይ በቅድሚያ ለተሰጠው ስራ በፈቃዱ ይሰማራል፡ ፡ አገልጋዩን የሚያሳስበው፡-

- ወንጌልን ላልዳኑ ማድረስ
- የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት እና የስብከት ዝግጅት

- አስተዳደር
- የመጋቢዎች አገልግሎት ዘርፍ
- ቤተሰብ
- የግል ጊዜ
- ሌሎች ኃላፊነቶች

(ከEd Stetzer ፣ *Planting New Churches in a Postmodern Age* ከተሰኘ መጽሐፍ የተወሰደ)

## 3. ሌሎችን በአገልግሎት ውስጥ እንዲሳተፉ ማድረግ ይችላል

አገልጋዩ (የቤ.ተ.አ) እንዴት ሰዎችን በአገልግሎቱ እዲሳተፉ እና አገልግሎቱ የራሳቸው እደሆነ እዲሰማቸው እደሚያደርግ ያውቃል፡፡

አገልጋዩ ሰዎችን የተልዕኮው አንድ ክፍል አድርጎ ስለሚወስዳቸው ይህ አገልጋይ የሚተክለውን አዲስ ቤተክርስቲያን ራዕይ ሰዎች እንደራሳቸው አድርገው ለመስራት ይቀላቀሉታል፡፡

*"...አንድ ብቻ ከመሆን ሁለት መሆን ይሻላል፡፡"* መክ 4፡9

አደጋ ቤተክርስቲያን መትከልን ብቻ ከመመኘት የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋይን በብዛት ማፍራትን ከግምት ውስጥ ማስገባት አስፈላጊ ነው፡፡ ቤተክርስቲያን ተከላን ብቻ የምናስብ ከሆነ አገልጋዮች ሰዎችን ለራሳቸው ምኞት ማስፈጸሚያ መሳሪያ የሚሆኑ አገልጋዮች ብቻ አድርገው በመውሰድ፤ እግዚአብሔር የእርሱ ልጆች ለሆኑ ሁሉ ለእያንዳንዳቸው የሰጠውን ልዩ ልዩ ጸጋ ተጠቅመው ቤተክርስቲያንን እንዳያንጹ እንቅፋት ይሆናሉ፡፡

ቁልፍ በአንድ ቡድን ውስጥ በመስራት፤ በጥሩም ይሁን በመጥፎ ጊዜ ሰዎች አንዳቸው በሌላቸው ላይ የሚተማመኑና የሚደጋገፉ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

## 4. ያላመኑትን በወንጌል ይደርሳል

ቤተክርስቲያን የምንተክልበት ዋና አላማ የጠፉትን ለመፈለግ ከሆነ፤ እንግዲያውስ እነርሱ ያሉበት ድረስ መሄድ ያስፈልጋል፡፡

- አሳዎች የሚረቡበት ገንዳ ውስጥ ወይንም አሳ እንደጌጥ የሚቀመጥበት የመስታወት ሳጥን ውስጥ አሳ ለመያዝ መረብ መጣል አያስፈልግም፤ አናጠምድምም፡፡
- ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ እንዲህ ብሏቸው ነበር "ሰዎችን አጥማጆች እንድትሆኑ አደርጋችኋለሁ" ማቴ 4፡19፤ ማር 1፡17፤ ሉቃ 5፡10

**ዓሳ ለጌጥ ከሚታይበት ዕቃ ውስጥ ዓሳ የሚያሰግረው ሰው ምሳሌ፡-**
የቤተክርስቲያን ተከላ ያልዳኑ ወገኖችን ለመድረስ ከሆነ፤ እነርሱ በሚገኙበት አካባቢ ነው ልንተክለው የሚገባው፡፡ ዓሳ ለማስገር ወደ ዓሳ ማርቢያ ስፍራ አንሄድም ይልቁኑ ወደ ሐይቅ አካባቢ በመሄድ ነው የምናሰግረው፡፡ እያንዳንዱ የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋይ ሊጠይቀው የሚገባው ጥያቄ፤ እኔ የምፈልጋቸው "ዓሶች" የት ይገኛሉ? የሚለውን ነው፡፡ አዲስ አጥቢያ የሚፋፋው አዳዲስ አማኞችን በመጨመር መሆኑን ልብ በል፡፡ ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ እንዲህ አላቸው "ሰውን የምታጠምዱ አደርጋችኋለሁ" (ማቴ 4፡19፤ ማር 1፡17፤ ሉቃ 5፡10)፡፡ የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋዮች ውጤታማ፣ ጠቃሚ እና በወንጌል ስርጭት ዘይቤአቸው ወቅቱን የጠበቁ ይሆኑ ዘንድ ኢየሱስ የተናገረውን መረዳት እና አስፈላጊውን ባህርይ ማዳበር ይጠበቅባቸዋል፡፡



## 5. ባለትዳር ከሆነ፣ የትዳር አጋሩ ድጋፍ አይለየውም

ባለትዳር የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋይ በአገልግሎቱ የትዳር አጋሩ ሙሉ ድጋፍ ሊኖረው ያስፈልጋል፡፡ በዚህ አንዳቸው በሌላቸው አገልግሎት ውስጥ እንዴት መሳተፍ እንዳለባቸው ስምምነት ላይ መድረስ ያስፈልጋቸዋል፡፡ ምንም እንኳን የሚደጋገፉበት መንገድ እና ደረጃ ከአገልጋይ አገልጋይ የተለያየ ቢሆንም አገልጋዩ እና የትዳር አጋሩ ለአገልግሎቱ ቁርጠኛ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡

**የተለመደ፤ ነገር ግን  አደገኛ ስህተቶች**

አንድ የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋይ ሊሰራ ከሚችላቸው ስህተቶች ሁሉ የከፋ ስህተት የትዳር አጋሩን ሚና ዝቅ አድርጎ መመልከትና ለማሳተፍ ዳተኛ መሆን ነው፡፡ የቱንም ያህል ቤተክርስቲያን ተከላ አገልግሎት ስኬት የትዳርን መፍረስ ሊተካም ሆነ ሊያካክስ አይችልም፡፡ አንድ ግለሰብ በሁለት በኩል የተከፈተበትን ጦርነት፤ ከሁለት በአንዱ በኩል ያለውን ሳይሸነፍ ለረጅም ጊዜ መዋጋት አይችልም፡፡ ባለትዳር ከሆንክ ከትዳር አጋርህ ጋር ሳትስማማ በፍጹም ወደቤተክርስቲያን ተከላ አገልግሎት እንዳትሰማራ፡፡

**ከትዳር አጋርህ ጋር፡-**

ሀ. የትዳር አጋርህን/ሽን ስለቤተክርስቲያን ተከላ አገልግሎት ምን እንደሚሰማው/ማት እና ልታገለግልበት/ሊያገለግልበት የሚችለውን የአገልግሎት ዘርፍ በግልጽ ተወያዩ፡፡ በዚያውም ስለቤተክርስቲያን ተከላ አገልግሎት የማይመቻትን/ የማይመቸውን ጉዳይ አንስቶ መወያየት አስፈላጊ ነው፡፡ እናም እነዚህን ምቾት የሚነሱ ጉዳዮች እንዴት መወጣት እንደምትችሉ ተነጋገሩ፡፡

ለ. ከትዳር አጋርህ/ሽ ጋር በቤተክርስቲያን ተከላ አገልግሎት ውስጥ የእርሱ/ሷ ድርሻ ምን እንደሚሆን፤ ምንም እንኳን አገልግሎቱን ሙሉ ማድረግ የእኛ ብዙ ጊዜ የሚፈልግ እኳን ቢሆን በዚህ ውስጥ እዴት ትዳር ተንከባክቦ ማሳደግ እደሚቻል ተወያዩ፡፡

**6. ከሌሎች ጋር ህብረትን መመስረት ይችላል**

በቤተክርስቲያን ተከላ አገልግሎት ላይ የተሰማራ አገልጋይ ባለው የማህበራዊ ሕይወት ተሰጥኦ ከሌሎች ሰዎች ጋር ያለውን ህብረት በመመስረትና በማጠንከሩ ረገድ መልካም ተጽዕኖ የመፍጠር ችሎታ ይኖረዋል፡፡

አገልጋዩ ከእነዚህ ጋር በሚገባ ህብረት ያደርጋል፡-

- ከቤተክርስቲያን አመራር ቡድን ጋር
- በወንጌል መደረስ ከሚገባቸው ህዝቦች ጋር
- ከማህበረሰብ መሪዎች ጋር
- በማህበረሰቡ ውስጥ ከሚገኙ ሰዎች ጋር
- ከሌሎች መሪዎች ጋር

ሰዎች ለእነርሱ ምንያህል ግድ እደሚልህ እስኪያውቁ ድረስ የአንተ የዕውቀት ብዛት ጉዳያቸው አይደለም፡፡

**7. ለቤተክርስቲያኒቱ ሁለንተናዊ እድገት ሁለንተናቸውን የሚሰጡ ናቸው**

ጤናማ ቤተክርስቲያን ለመትከል ራሱን የሰጠ አገልጋይ በሁለንተናዊ የቤተክርስቲያን እድገት ያምናል፡፡ እንዲህ ያለው አገልጋይ ከቁጥር እድገት ይልቅ የአካል እድገት እና የመንፈሳዊ ሕይወት እድገት ይፈልጋል፡፡

- ቤተክርስቲያን ከዚህ በታች በተዘረዘሩት መስኮች ማደግ አለባት፡
  1. የአማኞች <u>በመንፈሳዊ ሕይወት</u> ያድጋሉ፡፡
  2. ቤተክርስቲያን <u>እንደ አካል</u> ማደግ ይገባታል፡፡
  3. ቤተክርስቲያን <u>በቁጥር ብዛት</u> ማደግ ይገባታል፡፡
- **የክትትል ጠቀሜታ**

  የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋይ ቤተክርስቲያን በቅዱስ ቃሉ መሰረት በሁሉም መስክ “ሊተክላት” ይገባል፤ምክንያቱም ቤተክርስቲያን ወንጌልን መስበክ ብቻ ሳይሆን ያመኑትንም ደቀመዝሙር ማድረግ ስለሚጠበቅባት፡፡ ቤተክርስቲያን የወንጌልን ዘር መዝራት ብቻ ሳይሆን ዘሩን ለፍሬ ማብቃትም ተግባሯ ነው፡፡

  ልክ ሰጎን ጫጩቶቿን እንደምትረሳ፤ ሰነፍ የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋይም ደቀመዝሙር መሆን የሚገባቸው ሰዎች የሚፈልጉትን ክትትል ይነፍጋቸዋል፡፡ (ኢዮብ 39፡13-17)

## 8. ለማህበረሰቡ ፍላጎት ምላሽ ይሰጣል

የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋይ ማህበረሰቡ ምን እንደሚመስል ያውቃል የምትተከለው ቤተክርስቲያንም ማህበረሰቡን የምትመስል እንድትሆን ያደርጋል፡፡ ለማህረሰቡም ፍላጎት ምላሽ ይሰጣል፡፡ እንዲህ ሲያደርግ የሚያገለግለው ማህበረሰብ ምን እንደሚመስል በበለጠ እንዲያውከማገዙም በላይ ማህበረሰቡን እዴት ማገልገል እደሚችል ግንዛቤ ይኖረዋል፡፡ ያሉበትን ማህበረሰብ በትክክል የተረዱ እና በማንኛውም ማህበራዊ ሕይወት ከሰዎች ጋር የሚሳተፉ ማህበረምዕመናን በማህበረሰቡ ውስጥ ሰርገው የመግባት ከፍተኛ አቅም ስለሚኖራቸው ከፍተኛ ተቀባይነትን ያተርፋሉ፡፡

*“በዚያ ወራት ደግሞ ብዙ ሕዝብ ነበረ የሚበሉትም ስለሌላቸው ደቀ መዛሙርቱን ጠርቶ። ሕዝቡ ከእኔ ጋር እስካሁን ሦስት ቀን ውለዋልና የሚበሉት ስለሌላቸው አዝንላቸዋለሁ፡፡”* ማር 8፡1-2

ሊኖር የሚችል ፍላጎት፡-

- የቤተሰብ እና የትዳር ችግር
- የመጠጥ ሱስ
- ብቸኝነት
- የፍትህ እጦት
- ረሃብ ወይንም ድህነት
- መሃይምነት ወይንም የትምህርት እጥረት
- የመኖሪያ ቤት ችግር
- የስራ እድል እጦት
- ሌሎች.....

**አሳባችሁን ግለጹ፡-**

ቤተክርስቲያናችሁ በተተከለችበት አካባቢ በማህበረሰቡ ውስጥ በዚህ ወቅት ያለ እና እናንተ የምታውቁትን ፍላጎት ዘርዝሩ፡-

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

ከእነዚህ ውስጥ በጣም አንገብጋቢ የምትሏቸው የትኞቹ ናቸው፡-

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

የትኞቹን ፍላጎቶች መድረስ እንደሚያስፈልጋችሁ እንድትለዩ እግዚአብሔር እንዲረዳችሁ ጸልዩ፡፡ በዚህም የለያችሁትን ፍላጎት መድረስ የምትችሉበት ግብአት እግዚአብሔር እንዲያዘጋጅ ለምኑት፡፡

ማህበረሰቡን ለመድረስ የሚያስፈልጉ ግብአቶችን ዝርዝር ከዚህ በታች አስፍሩ፡-

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

## 9. የሌሎችን ጸጋ ይጠቀማል

ውጤታማ የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋይ የሌሎችን ጸጋ በተለያዩ አገልግሎት ክፍሎች ውስጥ እንዴት ባለ ሁኔታ መጠቀም እንዳለበት ያውቃል፡፡ ምዕመኑን በማነሳሳት እና እንደየጸጋቸው እንዲያገለግሉ እድሎችን በማመቻቸት ከፍያለ የአገልግሎት ውጤት ያመጣል፡፡

**ትግበራ፡-**

በዚህ ወቅት በእናንተ ቤተክርስቲያን የሚገኙና ጸጋቸውን ለይታችሁ ያወቃችኋቸውን ሰዎች ስም ዝርዝር ጻፉ፡-

| ግለሰብ | ስጦታ/ችሎታ |
|---|---|
| | |
| | |
| | |
| | |
| | |
| | |
| | |

የሰዎችን ጸጋ መለየት ቀላል ተግባር ነበር ወይንስ የእያንዳንዱን ሰው ጥሪ ለማወቅ የአገልግሎት እድል መስጠት አስፈልጓችሁ ነበር?

በተከላችሁት ቤተክርስቲያን ውስጥ ስለጸጋ ስጦታዎች አስተምሩና ከዚያም እያንዳንዱ ሰው ጸጋውን የሚለይበት እድል ስጡ፡፡

## 10. እንደየአስፈላጊነቱ አሳቡን የሚለውጥ

የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋይ ነገሮች ሁልጊዜ እንድታሰቡ እደማይፈፀሙ፤ እንደውም አማኝ ማህበረሰብን በመፍጠሩ ረገድ ከታቀደው በታች ሊሆኑ እንደሚችሉ ያውቃል፡፡ በዚህም ሁኔታው በሚፈቅደው መሰረት ለውጦችን ማድረግ የሚችል ነው፡፡

### ሁለት ጠቃሚ አስተያየቶች/ምክሮች

1. የምንሰራው ከሰዎች ጋር እንደመሆኑ፤ እያንዳንዱ ሰው የራሱ ፈቃድ፣ አሳብ እና ፍላጎት ስላለው እንደየአስፈላጊነቱ አሳብን መቀየር ከአገልጋዩ ይጠበቃል፡፡
2. አገልጋዩ የሌሎችን አሳብ መቀበልን እንደ ግዴታ መውሰድ የለበትም ምክንያቱም የሚሰጡን አሳቦች ውስጥ መልካምም መጥፎም ሊኖር ስለሚችል፡፡ የሌሎችን አሳብ ከግምት ውስጥ ለማስገባትና ለመቀበል ፈቃደኛ መሆን፤ ሌሎች የሚሰጡንን አስተያየቶች ሁሉ ተቀብለን ያለምንም ምርመራ ተግባራዊ እናደርጋለን ማለት አይደለም፡፡

### አሳባችሁን ግለጹ፡-

በቅርብ ጊዜ የገጠማችሁንና አሳባችሁን ለመቀየር ያበቃችሁን አንድ ሁኔታ ታስታውሳላችሁ? እንዴት ነው ነገሩን የተወጣችሁት? በጊዜው የሰጣችሁት ምላሽ አሁን ቢሆን መቀየር የምትፈልጉት አለ?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

## 11. በቤተክርስቲያን ውስጥ ያለን አንድነት ይጠብቃል

አገልጋዩ መሰጠትንና ህብረትን ለማጠናከር የሚረዳ ስፍራና ምቹ ሁኔታን እንዴት አድርጎ ማመቻቸት እንደሚችል ያውቃል፡፡ እንዴት አድርጎ ግጭቶችን ጤናማ በሆነ መንገድ መፍታት እደሚችል፣ ትዕግስትን በኑሮው ማሳየት፣ መልካም አድማጭነትን እና በሃሳብ ከማይስማማቸው ሰዎች ጋር እዴት በመከባበር መኖር እንደሚችል ያውቃል፡፡

*“እንዲሁ ብዙዎች ስንሆን በክርስቶስ አንድ አካል ነን፥ እርስ በርሳችንም እያንዳንዳችን የሌላው ብልቶች ነን።”* ሮሜ 12፡5

አገልጋዩ አዳዲስ መንጎችን ወደበረት ማምጣት ላይ ብቻ ትኩረት አያደርግም፤ ይልቁንም እነዚህን አዳዲስ መንጎች በአንድ አካል እንዴት እንደሚያስተሳስራቸውም ግድ ይለዋል፡፡ አንድ አካል በደህና ለማገልገል አንድ መሆንና የጋራ መግባባት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ቤተክርስቲያን እያንዳንዱ አማኝ ትብብር እና አንድነት የተመሰረተች ሲሆን ይህም ህብረት በአንድ እንዲጋጠም እና እንዲያገለግል አደረጃጀት፣ ምክንያት እና ዓላማ ያስፈልገዋል፡፡ የቤተክርስቲያን ጥንካሬ ያለው በአንድነት ውስጥ ነው፡፡

*ወንድሞች አንድ ይሁኑ*

*ምክንያቱም ይህ ቀዳሚው ትዕዛዝ ነውና፤*

*እውነተኛም ህብረት ይኑራቸው*

*በማንኛውም ጊዜ፤*

*ምክንያቱም በመካከላቸው መለያየት እና ጥል ካለ*

*ከውጭ ያሉ ነጥቀው ይበሏቸዋል፡፡ - ማርቲን ፊዬሮ*

## 12. እንደየአካባቢው አውድ ራሱን መለወጥ እና ማስማማት

አገልጋዩ የሚያገለግልበትን አካባቢ ይለምዳል ደግሞም ካለው አውድ ጋር ራሱን ያስማማል፡፡ ለሮማውያን ሮማዊ ለግሪኮች ደግሞ ግሪካዊ መሆን ይገባዋል (1ቆሮ 9፡19-21)፡፡

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የጢሞቴዎስ አባት ግሪካዊ እንደሆነ እያወቀ እንዲገረዝ ያደረገው የአይሁዳውያንን መንፈስ ለመጠበቅ ነው፡፡ መልካም የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋይ ዜግነቱን፣ ባህሉንና ምርጫውን፣ የሚያውቀውን አካባቢ እና በዙሪያው ያሉትን በመተው እና አስፈላጊ መስሎ የታየውን ለውጥ የጠፉትን ለመድረስ ሲል ሁሉን ይተዋል፡፡

*ከሁኔታ ጋር ራሱን ማላመድ የሚችል ዓሳ የመኖር እድሉ ሰፊ ነው፡- ውሃ በሚጠፋ ጊዜ በደረቀ ጭቃ ውስጥ ለወራት የመቆየት ብቃት ያላቸው የዓሳ ዝርያዎች አሉ፡፡ ሌላ የዓሳ ዝርያ ደግሞ ከአንድ ወንዝ ወደሌላ ወንዝ የመጓዝ ብቃት ያላቸው ናቸው፡፡ በተመሳሳይ የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋዩም ከከባቢው ጋር ራሱን ማላመድ ይጠበቅበታል፡፡*

ለምሳሌ፡- ከሁኔታ ጋር የሚለማመድ አሳ ሕይወቱን ማቆየት ይችላል፡፡

*“መዋረድንም አውቃለሁ መብዛትንም አውቃለሁ፤ በእያንዳንዱ ነገር በነገርም ሁሉ መጥገብንና መራብንም መብዛትንና መጉደልን ተምሬአለሁ።”* ፊሊ 4፡12

## 13.እምታቸውን በተግባር ያሳያሉ

ትክክለኛ አገልጋይ በራሱ ጥረት ሳይሆን በእግዚአብሔር ኃይል እንደሚኖር ያምናል፡፡ በዚህ አግዚአብሔር ለአገልግሎቱ መሳካት የሚያስፈልገውን እንደሚያዘጋጅለት በማመን እና በዚህም መሰረት በመኖር እምነቱን በተግባር ያሳያል፡፡

*“በመንፈሴ እንጂ በኃይልና በብርታት አይደለም ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር”* ዘካ 4፡6

- አንዳንዶች ለጌታ ብለው በሙሉ አቅማቸው ይሰራሉ፤ ነገር ግን የስራውን ጌታ ይረሱታል፡፡
- የምንፈልገው ውጤት ሁሌም በፍጥነት አይመጣም፤ በመሆኑም አገልጋዩ እግዚአብሔር በትክክለኛ ጊዜ ፍሬውን እንደሚያሳየው ማመን ያስፈልገዋል፡፡

**በዚህ ዝርዝር ውስጥ ያልገቡ ሌሎች ባህርያት**

ይህን ክፍለትምህርት ከመጀመራችን በፊት የዘረዘርናቸው የአገልጋይ ባህሪያትን አሁን ካየናቸው 13 ባህሪያት ጋር ሲተያዩ፤ በዚህ ያልተካተቱ ባህሪያት የትኞቹ ናቸው?

እነዚህን ዝርዝሮች በሚገባ ካስተዋልክ በኋላ በቤተክርስቲያን ተከላ አገልግሎት ውስጥ የትኞቹ ባህርያት በልዩነት በአገልግሎት ውስጥ ይታያሉ የትኞቹስ አይታዩም ( ስም መጥቀስ አያስፈልግም!)፡፡ ይህ ምን አይነት ልዩነት ያመጣል?

**ልምምድ | ራስን መገምገሚያ ቅጽ**

*መመሪያ፡-* ከ1-5 ያሉትን ቁጥሮች በመጠቀም ከዚህ በታች ባለው ሳጥን ውስጥ የተዘረዘሩትን በመመለስ እና ለራሳችሁ ነጥብ በመስጠት ራሳችሁን ገምግሙ፡፡

**1= በፍጹም አላውቅም 2= በረዥም የጊዜ ርቀት 3= አንዳንድ ጊዜ 4= በቋሚነት በየተወሰነ የጊዜ ርቀት 5= ሁልጊዜ**

| ባህርያት | ውጤት | ይህን ባህሪ ለማንጸባረቅ እንደምሳሌ የምትጠቅሰው አጋጣሚ |
|---|---|---|
| አገልግሎቱን በአይነህሊና ማሳየት እችላለሁ | | |
| ስለ(ራዕይ) የሚመጣ ነው | | |
| የራስ ተነሳሽነት አለኝ | | |
| ሌሎችንም በአገልግሎት አሳትፋለሁ | | |
| ያላመኑትን በወንጌል እደርሳለሁ | | |
| የትዳር አጋሬን ይሁንታ አግኝቻለሁ | | |
| ከሌሎች ጋር ግንኙነትን መመስረት እችላለሁ | | |
| ለቤተክርስቲያን እድገት የተሰጠሁ ነኝ | | |
| ላለሁበት ማህበረሰብ ምላሽ እሰጣለሁ | | |
| የሌሎችን ጸጋ መጠቀም እችላለሁ | | |
| እንደየአስፈላጊነቱ አሳቤን መቀየር እችላለሁ | | |
| የቤተክርስቲያንን አንድነት እጠብቃለሁ | | |
| ከሁኔታ ጋር የመስማማት ብቃት አለኝ | | |
| እምነቴን በተግባር አሳያለሁ | | |

## የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል | 1ጢሞ 3 እና ቲቶ 1

***ይህን መጠይቅ የምንጠቀምባቸው መንገዶች***

1. ከላይ በመጠይቁ ያገኘኸውን ውጤት ከምታምነው ግለሰብ ወይንም አገሊጋይ ለምሳሌ አንተን ከሚያሰለጥንህ ሰው፣ አባል የሆንበት ቤተክርስቲያን መሪ ወይንም ሌላ ከእኛ ጋር ከሚያገለግሉ ግለሰቦች አንዱን ለማማከር እና በእርግጥም ለቤተክርስቲያን ተከላ አገልግሎት በእርግጥ ጥሪያችን መሆኑን እና አለመሆኑን መገንዘብ እንችላለን፡፡ እናንተን በመምራት ላይ ያለውን አሰልጣኞቻችሁን ይህን መጠይቅ እንዲሞላ እና ውጤታማ ባልሆናችሁበት ክፍል እገዛውን እንዲሰጣችሁ ጠይቁ፡፡

2. በዚህ መጠይቅ ውስጥ በጣም የወረደ ውጤት ያገኛችሁባቸውን ሁለት ጥያቄዎች ለዩና እነዚህን ለማስተካከል ምን እንደሚጠበቅባችሁ በጽሑፍ አስፍሩ፡፡ ታዲያ የምትጽፏቸው መፍትሄዎች በአንድ ጉዳይ የሚያተኩሩ፣ ሊተገበሩ የሚችሉና ተግባሩን የምታጠናቅቁበት የተቆረጠ ጊዜ ያለው እንዲሆን ያስፈልጋል፡፡ በመጨረሻም ለአሰልጣኛችሁ አቅርቡት፡፡

**ማጠቃለያ፡-**

- በቤተክርስቲያን ተከላ አገልግሎት የተሰማሩ የተለያዩ አገልጋዮች፤ የተሳካላቸውም ይሁኑ ያልተሳካላቸው፤ የእነዚህ አገልጋዮች ልምድ እግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋዮች ሊኖራቸው የሚገባውን ባህሪ ለማወቅ ይረዳናል፡፡
- አንድ ማሰብ ያለብን ጉዳይ በምንመካበት ጌታችን የተሰጠን የቤተክርስቲያን ተከላ አገልግሎት እግዚአብሔር ራሱ የሚሳተፍበት መሆኑ ነው፡፡ ይህ ተግባር በአገልጋዩ በሚገለጡ የተወሰኑ ባህሪያት ላይ የሚደገፍ አይደለም፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለው "እንግዲያስ የሚያሳድግ እግዚአብሔር እንጂ የሚተክል ቢሆን ወይም የሚያጠጣ ቢሆን አንዳች አይደለም።" 1ቆሮ 3፡7 ቤተክርስቲያን መትከል የምንችለው ከእግዚአብሔር ጋር ተስማምተን መስራት ስንችል ብቻ ነው፤ እርሱ ቤተክርስቲያኑን ይሰራል፡፡ የቱንም ያህል አገልጋዩ የሰለጠነ ቢሆን፤ የቱንም ያህል በጥልቀት የተተከለችውን ቤተክርስቲያን አሰራር በመመዘን፤ እግዚአብሔር የቤተክርስቲያኒቱን ራስ ካልሆነ በአገልግሎቱ ምንም አይነት ውጤት ማምጣት አይችልም፡፡ እርሱ ክብርም ምስጋናም ይገባዋል፡፡

# ክፍለ ትምህርት 3

# ልንተክለው ያሰብነው ቤተክርስቲያን ምንይመስላል?

## ዓላማ

የዚህ ክፍለትምህርት ዓላማ የጤናማ ቤተክርስቲያን አስፈላጊ ባህሪያትንና የቤተክርስቲያን ተከላ አገልግሎት ግብን በዝርዝር ማስረዳት ነው፡፡ በቅድሚያ የአንድ ጤናማ ቤተክርስቲያን አምስት መሰረታዊ ግዴታዎችን ካነሳን በኋላ ሌሎች አምስት ተግባሮችን እናንሳና በእነዚህ ሁሉ ውስጥ ለጤናማ ቤተክርስቲያን የሚያስፈልገውን የመሪነት አይነት ትኩረት ሰጥቶ ማስረዳት የዚህ ክፍለ ትምህርት ዓለማ ነው፡፡

ቀለም ቀቢውና የሕንጻ ንድፍ ሰሪው፡- Stephen Covey የተባለ ሰው *The 7 Characteristics of Highly Effective People* በተሰኘ መጽሐፉ አንድን ፕሮጀክት በአምሮአችን አጠናቀን አስበነው መጀመር ስላለው ጠቀሜታ ያወሳል፡፡ አንድ ቀለም ቀቢ ቤቱን ቀለም ከመቀባቱ በፊት የቤቱ ቅብ ምን ሊመስል እንደሚችል የሚያሳይበት በአሳቡ ውስጥ የተቀመጠ ንድፍ አለ፡፡ ቀለም ቅቡን የሚጀምረው ጥንቅቅ አድርጎ ካሰበው በኋላ ነው፡፡ ልክ እንዲሁ አንድን ቤት ለመገንባት ቀድሞ የሕንጻ ንድፍ አውጪው ፕላኑን በወረቀት ላይ ያሰፍረዋል፡፡ እርሱም ጥንቅቅ አድርጎ በአሳቡ የጨረሰውን ነው ለመስራት የሚጀምረው፡፡ በቤተክርስቲያን ተከላ አገልግሎትም ቢሆን ግባችን ምን እንደሆነ አሳቡ ሊኖረን ግድ ነው፡ምንድን ነው ዒላማ አድርገን የተነሳነው? ምን አይነት መደምደሚያ ላይ ለመድረስ ነው እየሰራን ያለነው? በምንተክለው ቤተክርስቲያን ውስጥ አባላት የሚሆኑ ሰዎች ምን አይነት የሕይወት ምልልስ ሊኖራቸው ይችላል? የምታድግ እና ጤነማ ቤተክርስቲያን ግብአቶች ምንድን ናቸው?

**በአእምሮህ ሙሉ ስራውን አስበህ ስትጨርስ ጀምር** **ትግበራጡን**

- የቀስተኛው ትርክት፡- አንዳድ ሰዎች ወዳገኙበት ተወርውሮ በተሰካው ቀስት ዙሪያ ኢላማውን ያከ
- ለምሳሌ፡- ሰአሊ እና አርክቴክት

በቤተክርስቲያን ተከላ አገልግሎት፤ መጨረሻውን ማወቅ ጠቃሚ ነው፡፡



- ቀስታችንን ወዴት ነው የምንወነጭፈው?
- የምንሰራው ስራ ምን አይነት ፍጻሜ አለው?
- ጤናማ እና የሚያድግ ቤተክርስቲያን ለመመስረት የሚያስፈልጉ ግብአቶች ምንድን ናቸው?

ቀጥሎ የምንመለከተው አዳዲስ ቤተክርስቲያናትን ለመመስረት ጠቃሚ የሆኑ የተልዕኮ እና አደረጃጀት ሞዴል እንመለከታለን፡፡

**የመክፈቻ ተግባር** | የጤናማ ቤተክርስቲያን ወሳኝ ምልክቶች

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡-** ተሳታፊዎችን በሁለት ቡድን በመመደብ፤ አንዱ ቡድን ጤናማ ቤተክርስቲያናት የሚያንጸባርቁትን ባህርያት፤ ሁለተኛው ቡድን ደግ ጤናማ ያልሆነ ቤተክርስያን ዬያንጸባርቀውን ባህርይ እንዲጽፉ አድርግ፤ ከዚያ የሁለቱንም ዝርዝር ለጠቅላላው ተሳታፊ አንብብ፡፡ ከዚህ ተግባር ተሳታፊዎች ምን ይገነዘባሉ?

ትርጓሜውን ማንበብ እና ይህን ለማስረዳት ደግሞ የራስህን ልምድ መጠቀም ትችላለህ ይሁን እንጂ ይህ ክፍለትምህርት ያለው ጊዜ አጠር ያለ ስለሆነ ከእነዚህ ነጥቦች በየትኛውም ላይ ሰፊ ጊዜ ወስደህ ማስረዳት አይኖርብህም፡፡

## የጤናማ ቤተክርስቲያን ምልክቶች

*“እንግዲያስ ከእንግዲህ ወዲህ ከቅዱሳን ጋር ባላገሮችና የእግዚአብሔር ቤተ ሰዎች ናችሁ እንጂ እንግዶችና መጻተኞች አይደላችሁም። በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንጻችኋል፥ የማዕዘኑም ራስ ድንጋይ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፤ በእርሱም ሕንጻ ሁሉ እየተጋጠመ በጌታ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንዲሆን ያድጋል” ኤፌ* 2፡19-21

በማስከተል የምንመለከተው የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋዩ መጨረሻውን ከመጀመሪያው አስቦ እንዲነሳ የሚረዳውን የድርጅትና የተለዕኮ ዕቅድ ነው፡፡ ከታች ያለው ስዕላዊ መግለጫ ከማህበረ ምዕመኑ የሚጠበቁ አምስቱን ግዴታዎች እና አምስቱን ተግባራት በተለየ አውድ ሁሉንም የሚያሳይ ነው፡፡




ጤናማ ቤተክርስቲያን ያለችበትን ማህበረሰብ በክርስቶስ ኢየሱስ ስም በማገልገል ለውጥን ታመጣለች፡፡ ሰዎችን ወደክርስቶስ መጥራት ብቻ ሳይሆን ከእርሱ ጋር (በእርሱ) እንዲኖሩ ትረዳለች፡፡ እያንዳንዱ ቤተክርስቲያን የራሱ የሆነ ማንነትና ለየት ያለ የጸጋ ስጦታዎች ስብጥር ኖሮት የሚያድግ የእግዚአብሔር ቤተሰብ ይሆናል፡፡ ጤናማ ቤተክርስቲያናት የማህበረሰቡን ፍላጎት ለማሟላትና ለእግዚአብሔር ክብርን ለማምጣት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የበረቱ ናቸው፡፡

## አምስቱ ቁልፍ ግዴታዎች

1. **ግልጽ እና አነቃቂ ራዕይ**
   ፍቺ/ትርጉም ራዕይ ማለት እግዚአብሔር የእርሱን የመዋጀት አላማ በእናንተ እንዴት እንደሚፈጽም ሊመጣ ያለውን (የወደፊቱን) መመልከት ነው፡፡

*“ራዕይ እግዚአብሔር እንድንሰራው እና እንዲሆንለት የሚፈልገውን ቤተክርስቲያን አጥርታ እድታይ የሚያግዝ፤ በዚህም የክርስቶስ አካል በአንድነት በእግዚአብሔር የተፈጠረውን አዲሱን ሰው ታሳይ ዘንድ የሚያስችል ነው፡፡”*

-Tim Koster and John Wagenveld, *Take Your Church’s Pulse*

የተሰማችሁን ግለጹ  እናንተ የምትተክሏት ቤተክርስቲያን ምን እንድትመስል እና ምን እንድትሰራ እግዚአብሔር ይፈልጋል? አዲስ ከተከላችኋት ቤተክርስቲያን መሪዎች ጋር የቤተክርስቲያኒቱን ራዕይ ወይንም እግዚአብሔር እደቤተክርስቲያን ሲጠራችሁ እንድትሆኑለት እና እንድትሰሩለት የፈለገውን በአጭሩ ጽፋችሁ አስቀምጡ፡፡ ይህንንም ትኩረት ሰጥታችሁ የምትሰሩበት የአገልግሎታችሁ አቅጣጫ አድርጉት፡፡

## 2. መሪዎችን ማንቀሳቀስ

**ፍቺ/ትርጉም** | አውብሪይ ማልፈርስ የተባለ ጸሐፊ በተሰኘ *Planting Growing Churches for the 21st Century* መጽሐፉ መሪነትን እንደሚከተለው ፈትቶታል/ተርጉሞታል፡- "ክርስቲያን መሪዎች ለእግዚአብሔር (ባህሪይ) የቆረጡ፤ ወዴት እንደሚሔዱ የሚያውቁ(ራዕይ) እና ተከታዮች ያሏቸው ናቸው (ተጽዕኖ ፈጣሪ)፡፡" አንድን ሰው ለቤተክርስቲያን ተከላ አገልግሎት ስንሾም፤ የመሪነት ክህሎቱን ማሳደግ የሚችልበትን መንገድ አብሮ ማሰብ ያስፈልጋል፡፡

*"መሪዎች ራዕዩን የተረዱ እና ራዕዩን የሚኖሩ፣ ለማህበረ ምዕመናቸው ራዕዩን በትክክል ማስተላለፍ የሚችሉ እና ቤተክርስቲያንን ለራዕዩ እውን መሆን እንደ አንድ አካል የሚያንቀሳቅሱ ናቸው"*

-Tim Koster and John Wagenveld, *Take Your Church's Pulse*

በሽለቆ ውስጥ የሚያልፈው ባቡር፡- የሚተካውን አገልጋይ ያላሰለጠነ፣ ሁሉንም የቤተክርስቲያን ስራ በራሱ የሚሰራ እና አንድ ከሰዓት በኋላ እንኳን የማያርፍ አንድ የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋይ ነበር፡፡ በጣም ስለተዳከመ ከቤተክርስቲያን አንድ ሰኞ ከሰዓት ረፍት ጠይቆ ተፈቀደለት፡፡ታዲያ በዚህ ቀን ያደረገው ነገር ቢኖር ወንበር ይዞ ወደ አንድ ከፍ ወዳለ ተራራ ወጥቶ ተቀመጠ፡፡ እናም የሚያደርገውን ነገር ለማወቅ የጓጉ የቤተክርስቲያኒቱ አባሎች ምን እያደረገ እንደሆነ ሲጠይቁት፤ እንዲህ ብሎ መለሰላቸው፤ ሁሌም በዕረፍት ጊዜዬ ይህን ባቡር ሲያልፍ ማየት ያስደስተኛል፤ ምክንያቱም የእኔን ግፊ ሳይጠብቅ በራሱ የሚጓዝ አንድ ነገር ይህ ባቡር ስለሆነ፡፡ ይህ መጋቢ የሚተኩትን አገልጋዮች ስላላሰለጠነ፤ የደረሰበትን መከራ እየተቀበለ እንዳለ እንመለከታለን፡፡

**መግቢያ**| ጳውሎስ አብሮ ሰራተኞችን እንዴት ነው ያሳደገው? 2ጢሞ 2፡2 ለሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ፤ቤተክርስቲያን በቋሚነት ትኖር ዘንድ ለእያንዳንዱ አጥቢያ ቤተክርስቲያን መሪን ማሳደግ አጅግ አስፈላጊ ነገር ነበር፤ ለዚህም ነው እንዲህ ያደረገው፡-

1. ለመሪዎች ቦታ ይሰጥ ነበር፤ በስራው ላይም ይሾማቸው ነበር፡፡
2. እነርሱን ለማዘጋጀት ቁርጠኛ ነበር፡፡
3. ያምናቸው ነበር፡፡

**ሁለቱ አደጋዎች**

**1. የመሲህነት ፍላጎት ምልክት**

ይህ ችግር ጳውሎስ በተግባር ከኖረው ፍጹም ተቃራኒ ነው፡፡ ጳውሎስ መሪዎችን ለማፍራት የተጠቀመበት መንገድ እንደአንቀሳቃሽ ሞተር ተድርጎ ቢወሰድ የመሲህነት በሽታ ደግሞ የመሪነትን ስልጠና የሚቃወም እንቅፋት አድርገን ልንወስደው እንችላለን፡፡ የበሽታው ምልክቶች ግልጽ እና በቀላሉ ልንለያቸው የምንችላቸው ናቸው፡፡

ሀ. እኔ መተኪያ የሌለኝ ነኝ ብሎ ማሰብ፡፡

ምሳሌ፡- ሙሴ (ዘጸ 13፡13-27)

ለ. የሌሎች ፍላጎት ሁልጊዜም ከእኔ ፍላጎት ይቀድማል ብሎ ማመን፡፡

እዴት ነው ይህን በሽታ መቋቋም የምንችለው?

እርምጃ 1 ለችግሩ መኖር ዕውቅና ይሰጣል

እርምጃ 2 የተማሪውን አመለካከት ምን ሊሆን እንደሚችል ይገምታል

እርምጃ 3 የእግዚአብሔር ስራ በእኛ ውስጥ ይፈልጋል

**2. "ሁሉን እኔ ልከውን" ባይ አገልጋይ**

"በሸለቆ ውስጥ የሚያልፈው ባቡር" የተሰኘው ታሪክ የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋዩ ሁሉንም የመሪነት ስፍራዎች በባለቤትነት ሲቆጣጠራቸውና በአዲሲቷ ቤተክርስቲያን ውስጥ የሚከናወን እያንዳንዱ ጉዳይ በቀጥታ በእርሱ ቁጥጥር እዲሆኑ ሲያደርግ የሚከሰትን አደጋ ያሳያል፡፡

**አራቱ የመጽሐፍ ቅዱሳዊ መሪነት ባህሪያት**

ዶ/ር ዴቪድ ራሚሬዝ አራት ቁልፍ የአዲስ ኪዳን የመሪነት ምልከቶችን ያሳየናል፡

***ሀ. መሪ እንደ ሐዋርያ*** | ሮሜ 1፡1-5፡፡ ወንጌል ከዚህ ቀደም ወዳልደረሰባቸው ህዝቦች እና ቦታዎች የተላከ፡፡

***ለ. መሪ እንደ አገልጋይ*** | ማር 10፡45፤ ፊሊ 1፡1 በትህትና እና በፍቅር ማገልገል፡፡

***መ. መሪ እንደ ባለራዕይ*** | ኤፌ 1፡17 እግዚአብሔር በማህበረሰብ ውስጥ ሊሰራ ያለውን ማየት/መገንዘብ

***ሰ. መሪ እንደ አበረታች እና አስታጣቂ*** | ኤፌ 4፡11-12 ሌሎች ለአገልግሎት ማዘጋጀት፡፡

**3. የአገልግሎት ክፍሎችን ማነቃቃት**

ፍቺ/ትርጉም *"የቤተክርስቲያኒቱ አባላት አንድ ሆነው፣ ጸጋቸውን ተጠቅመው ማህበረ-ምዕመኑን እና ማህበረሰቡን ለማገልገል ሲሰሩ ማነቃቂያ ይባላል"*
-Tim Koster and John Wagenveld,
*Take Your Church's Pulse*

*"ልዩ ልዩን የእግዚአብሔርን ጸጋ ደጋግ መጋቢዎች እንደ መሆናችሁ፥ እያንዳንዳችሁ የጸጋን ስጦታ እንደ ተቀበላችሁ መጠን በዚያው ጸጋ እርስ በርሳችሁ አገልግሉ፤ ማንም ሰው የሚናገር ቢሆን፥ እንደ እግዚአብሔር ቃል ይናገር፤ የሚያገለግልም ቢሆን፥ እግዚአብሔር በሚሰጠኝ ኃይል ነው ብሎ ያገልግል፤ ክብርና ሥልጣን እስከ ዘላለም ድረስ ለእርሱ በሚሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል እግዚአብሔር በነገር ሁሉ ይከብር ዘንድ፤ አሜን"* 1ጴጥ 4፡10-11

**አምስቱ የትግበራ ደረጃዎች**

1.ሀሉንም አባላት ለማንቀሳቀስ መሪዎችን አዘጋጅ፡፡
2.ስለ ጸጋ ስጦታዎች እና የባለአደራ መሪ ችሎታ አስተምር፡፡
3.የእያንዳንዱን አባል ስጦታውን እና ሊሰማራበት የሚፈልገውን ለይ፡፡

4. እያዳንዱን ምዕመን በአገልግሎት ወይንም በ ግልጋሎት አካባቢ እንዲሰራ ሹም/ ቦታ ስጥ፡፡
5. የቤተክርስቲያኒቱ የተለያዩ ስፍራዎች እንዴትእንደሚሰሩ እንቅስቃሴአቸውን በማጤን እና በአትኩሮት በመከታተል አስፈላጊውን ማሻሻያ ማድረግ፡፡

*"Use your ministry to build people,*
*not people to build your ministry."*
*- Jacqueline Heasley*

## 4. እውነተኛ የግብአት ባለአደራ

**ፍቺ/ትርጉም** | ቤተክርስቲያን የመልካም ባለአደራ ምሳሌ በመሆን ማህበረ ምዕመኗ ባላቸው ሃብት፣ ንብረት እና ለሕይወት አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች (ጊዜ፣ ችሎታ/ስጦታ እና ድብቅ ሃብት) እንዴት መጠበቅ እንዳለባቸው እዲያስቡ ማነቃቃት ያስፈልጋታል፡፡ በዚህም እንዚህን ግብቸአቶች እና ያላቸውን የገንዘብ ስጦታ በመጠቀም የእግዚአብሔርን መንግስት በቤተክርስቲያናቸውና በሚኖሩበት ማህበረሰብ ውስጥ ግቡን ይመታ ዘንድ እዲጠቀሙበት ማነቃቃት፡፡
*"እግዚአብሔርን ከሀብትህ አክብር፥ ከፍሬህም ሁሉ በኵራት ጐተራህም እህልን ይሞላል፥ መጥመቂያህም በወይን ጠጅ ምልታ ትትረፈረፋለች።"* ምሳ 3፡9-10

### እዴት ነው ለቤተክርስቲያን ተከላ ገንዘብ ላገኝ የምችለው?

አንድ ሰው ቤተክርስቲያን ይተክል ዘንድ በእግዚአብሔር እንደተጠራ ሲያውቅ እና ሲያምን መጀመሪያ ከሚመጡ ጥያቄዎች ውስጥ አንዱ "የዚሕችን ቤተክርስቲያን ውልደት እና እድገት እውን የሚያደርግ የገንዘብ ምንጭ እንዴት አገኛለሁ የሚለው ነው፡፡" ይህን በተመለከተ ሁለት አስፈላጊ ንድፈአሳቦች አሉ፡
፡

1. በእግዚአብሔር መታመን፤ በእግዚአብሔር እንታመናለን? ፊሊ 4፡6-7፣ 19
2. መርካት፤ እግዚአብሔር የሚያስፈልገንን ሁሉ ሊሞላብን እንጂ የምንፈልገውን ሁሉ ሊሰጠን ቃል አልገባልንም፡፡ ፊሊ 4፡11-13

### አዲስ ቤተክርስቲያን ተከላን በገንዘብ የመደገፍ መንገዶች

1. አዲሲቱን ቤተክርስቲያን ከምታሰለጥነው ቤተክርስቲያን ድጋፍ ማግኘት
2. ከእምነት ተቋማት፣ በወንጌል ተልዕኮ ላይ ከሚሰሩ ሚኒስትሪዎች ወይንም ከድርጅቶች
3. አገልግሎቱን ለመደገፍ ከተቋቋሙ ገንዘብ አሰባሳቢ ኮሚቴዎች
4. ከጓደኛ፣ ቤተሰብ እና ኢንቨስተሮች የሚገኝ እርዳታ
5. ንብረትን በመሸጥ የሚገኝ ድጋፍ
6. ቤት ውስጥ ሁለት ሰዎች ስራ ይሰሩ እደሆነ የአንዳቸውን ደሞዝ ለአገልግሎቱ ማዋል
7. ባለሁለት ሙያ አገልጋይ

*"ቀን መቁጠሪያ እና የተሰራን እና ያልተሰራን የምንመዘግብበት ቅጾች ስነመለኮታዊ ዶሴዎች ናቸው፤ ማን እንደሆን እና ማንን እንደምናመልክ ይነግሩና" -Brian Kluth*

*"ሰው በሶስት የንግግር ወይንም ውይይት መንገዶች ያልፋል፤ በጭንቅላቱ፣ በልቡ እና በኪሱ፡፡ እንዳለመታደል ሆኖ ሁሉም በአንድ ጊዜ አይከሰቱም!"*
*-Martin Luther*

**አሳባችሁን ግለጹ** | እንዴት ነው የምትተክለው ቤተክርስቲያን የገንዘብ ድጋፍ እድታገኝ የምትሰራው? እንዴት ነው ምዕመኑን ስለአስራት የምታስተምረው?

### 5. መልዕክትን እና አውድን ማዋደድ/ማዋሃድ

**ፍቺ/ትርጉም** | ጤናማ ቤተክርስቲያን አውድን (መልክአምድራዊ መገኛን፣ ማህበራዊ እና ኢኮነሚያዊ ሁኔታዎችን፣ ባህልን እና የመሳሰሉትን...) ታሳቢ ታደርጋለች፡፡ በክርስቶስ ኢየሱስ የሆነው የወንጌላችን መልዕክት የማይለዋወጥ ሆኖ፤ እርሱን ለሌሎች የምንሰብክበት መንገድ ግን ይለዋወጣል፡፡

*"የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል።"* **2ጢሞ 3፡16-17**

**አምስቱ ቁልፍ ተግባራት | ባለአምስት ኮከብ ቤተክርስቲያን**

### 1. ወንጌል ስርጭትን የምታበረታታ

ፍቺ/ትርጉም | "ቤተክርስቲያን የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቲስን ወንጌል በቃል እና በተግባር በመንገርና በመኖር ሰዎች የእግዚአብሔር መንግስት አካል ይሆኑ ዘንድ ሰውን ሁሉ ትጋብዛለች፡፡"
-Tim Koster and John Wagenveld,
*Take Your Church's Pulse*

*"ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፥ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ።"* ሐዋ 1፡8

*"ጌታም የሚድኑትን ዕለት ዕለት በእነርሱ ላይ ይጨምር ጌታም የሚድኑትን ዕለት ዕለት በእነርሱ ላይ ይጨምር"* ሐዋ 2፡47

**የኢግል መለኪያ፡-** ይህ መለኪያ ሰዎች ራሳቸውን ለክርስቶስ ለመስጠት የሚያልፋበትን ሂደት እና በክርስትና ሕይወታቸው ወደፊት የሚሄዱበትን የሚያሳይ ነው፡፡

**የኢግል መለኪያ፡-** ወንጌል ስርጭት

-8 ግለሰቡ አንድ ልዕለ ኃያል እንዳለ ያውቃል

-7 ግለሰቡ ስለወንጌል የመስማት ጥቂት እድል አግኝቷል

-6 ግለሰቡ የወንጌልን መሰረታዊያን መረዳት ጀምሯል

-5 ግለሰቡ ወንጌል በግል ለእርሱ እንዴት ሊጠቅመው እንደሚችል መረዳት ጀምሯል

-4 ግለሰቡ ለወንጌል ቀና አመለካከት አዳብሯል

-3 ግለሰቡ ክርስትናን መከተል ምን አይነት ዋጋ እንደሚጠይቅ መረዳት ጀምሯል

-2 ግለሰቡ ወደ እምነት እርምጃን መውሰድ ጀምሯል

-1 ግለሰቡ ስለኃጢአቱ ንስሃ በመግባት ሕይወቱን ለክርስቶስ ለመስጠት በእምነት መንገድ ጀምሯል

**የኢግል መለኪያ፡-** ዳግም ልደት +1ግለሰቡ በአየሱስ ክርስቶስ ውስጥ ሆኖ የጀመረውን የሕይወት ጉዞ ይመዝናል +2ግለሰቡ በክርስቶስ አካል ውስጥ ይታቀፋል

+3ግለሰቡ የደቀመዝሙርነት እና የግልጋሎት ሕይወትን ይጀምራል

- የኢንግል መለኪያ
- ቀን መቁጠሪያ እና የተግባር መቆጣጠሪያ፤ እንዚህ ዶሴዎች ቤተክርስቲያን በእርግጥ ለወንጌል ስርጭት የተሰጠችና ቁርጠኛ የሆነች መሆን አለመሆኗን እንድናረጋግጥ ይረዱናል፡፡

"ታላቁ ተልዕኮ እንዴሁኔታው እንድንቀበለው በአማራጭነት የተቀመጠ ሳይሆን፤ እንድንታዘዘው የተደነገገ መለኮታዊ ትዕዛዝ ነው፡፡" *-Hudson Taylor (missionary to China)*

## 2. ሁሉን አቀፍ የደቀመዝሙርነት ስልጠና

**ፍቺ/ትርጉም|** *"ቤተክርስቲያን ሰዎች ኢየሱስን ጥርት አድርገው እንዲያዩትና ስለሕይወታቸው የእርሱ ፈቃድ ምን እንደሆነ እንዲያውቁ ታግዛለች፤ ይህም በሁሉም የሕይወት ዘርፍ ኢየሱስን እንዲከተሉ ትጥቅ ይሆናቸዋል፡፡"*

-Tim Koster and John Wagenveld,
*Take Your Church's Pulse*


*"ነገር ግን በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና እውቀት እደጉ። ለእርሱ አሁንም እስከ ዘላለምም ቀን ድረስ ክብር ይሁን፤ አሜን።"* 1ጴጥ 3፡18

*"በሐዋርያትም ትምህርትና በኅብረት እንጀራውንም በመቍረስ በየጸሎቱም ይተጉ ነበር።"* ሐዋ 2፡42


**የደቀመዝሙርነት አራቱ ቁልፍ ቃላት**

1. ስርአት.
2. ባህርይ.
3. የወንጌሉ ይዘት.
4. መሰጠት.

**ስዕላዊ መግለጫ |** የተከፋፈለ እምነት ከ ሁሉን ያዋደደ እምነት




የተከፋፈለ እምነት




ሁሉን ያዋደደ እምነት

**አሳባችሁን ግለጹ**

የእናንተ ቤተክረስቲያን ምዕመናን የትኛውን የሕይወት ክፍላቸውን በክርስቶስ ካለ እምነት ጋር ማቆራኘት ይጠበቅባቸዋል?

እንዴት ነው እናንተ በማቆራኘቱ ሂደት የምትረዷቸው?

**ስዕላዊ መግለጫ** | *መጽሐፍ ቅዱሳዊው ዓለም እና የሕይወት ንጽረት/ምልከታ፡- የደቀመዝሙርነት መሰረቶች*




ስለእግዚአብሔር፣ ስለዓለም፣ እና ስለማንነታችን ከቅዱስ ቃሉ በበለጠ በተማርን ቁጥር፤ እያንዳንዱ የሕይወታችን ክፍል ለእግዚአብሔር ይገዛ ዘንድ በፊቱ ለማቅረብ እንገደዳለን፡ደቀመዝሙርነት ማለት እንደዚህ ነው፡- ስለእግዚአብሔር፣ ስለቃሉ እና ስለማንነታችን ያለን እውቀት ማደግና በማንኛውም ሁኔታ እንደእግዚአብሔር ሕዝብ መኖር፡፡

"ሰዎች እጣፈንታቸውን አይወስኑም፤ ልማዳቸው ምን መሆን እንዳለበት ግን ይወስናሉ፤ ልማዳቸውም የወደፊት እጣፈንታቸውን ይወስናል፡፡" *ምንጩ የማይታወቅ*

"ስነመለኮት የሚያስተምሩ በቅድሚያ በሕይወታቸው ሊያስተምሩ ይገባል... እንዲህ ካልሆነ ግን በአንድ እጃቸው የገነቡትን በሌላኛው ያፈርሱታል፡፡" *-Matthew Henry*

### 3. በርህራሄ የተሞላ አገልግሎት

**ፍቺ/ትርጉም** | ቤተክርስቲያን የህዝብን ፍላጎት በክርስቶስ ኢየሱስ ስም እየደረሰች የእርሱ ደቀመዛሙርት ይሆኑ ዘንድ ትጋብዛለች፡፡

*"ያላቸውንም ሁሉ አንድነት አደረጉ። መሬታቸውንና ጥሪታቸውንም እየሸጡ፥ ማንኛውም እንደሚፈልግ ለሁሉ ያካፍሉት ነበር። ... እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ በሕዝብ ሁሉ ፊት ሞገስ ነበራቸው።"* ሐዋ 2፡45፣47

**በወንጌል ስርጭት እና በአገልግሎት መካከል ሶስት አይነት ግንኙነቶች አሉ**

1. አገልግሎት ለወንጌል ስርጭት እንደ<u>      ውጤት  </u>ሲወሰድ፡- ጌታን መቀበላችን ለሌሎች ወገኖቻችን ፍላጎት ይሞላ ዘንድ ንቁ ያደርገናል፡፡
2. አገልግሎት ለወንጌል ስርጭት እንደ<u>     ድልድይ   </u> ሲሆን፡- ሌሎችን ወንጌልን በቆይታ ለመስማት ፈቃደኛ ይሆኑ ዘንድ ቀድሞ እነርሱን ማገልገል፡፡
3. አገልግሎት ወንጌል ስርጭትን<u> ያግዛል     </u>፡- ሌሎችን በማገልገል ሂደት ውስጥ ስለኢየሱስ መናገር፡፡

"ሊኖሩት የሚገባ ሕይወት፤ ለሰው የሚኖሩበትን ሕይወት ብቻ ነው" *-Albert Einstein*

"ሰዎች ከሚሰሩት እና ሊሰሩ ከሚችሉት ስህተት ሁሉ የከፋ ስህተት፤ እኔ ማድረግ የምችለው ጥቂት ነው በማለት፤ የግል የመከወን ብቃትን ዝቅ አድርጎ በመመልከት ምንም ሳይሰሩ ማለፍ ነው" - Edmund Burke

### 4. ተንከባካቢ እና ሰውን በደስታ የሚቀበል ማህረሰብ

**ፍቺ/ትርጉም** | ማህበረ ምዕመኑ አንዱ የሌላውን ሸክም በመሸከም፤ የክርስቶስን ፍቅር እና ርህራሄ ማሳየት፡፡

"...በኅብረት...ይተጉ ነበር። ያመኑትም ሁሉ አብረው ነበሩ፤ በየቀኑም በአንድ ልብ ሆነው በመቅደስ እየተጉ ... በደስታና በጥሩ ልብ..." ሐዋ 2፡42፣44፣46

**ዮሐ 2፡17፡20-23** | የቤተክርስቲያን አንድነት የተመሰረተው በኢየሱስ እና በእግዚአብሔር አብ አንድነት ላይ ነው፡፡ ይህ የክርስቶስ ምስክርነት ነው ዛሬም ቤተክርስቲያንን ለተልዕኮዋ የሚያንቀሳቅሳት ኃይል የሆነው፡፡

**ትናንሽ የመጽሐፍቅዱስ ጥናት ቡድኖች** | እንዲህ ያሉ ቡድኖች እንዲቋቋሙ እድሎችን በመስጠት ምዕምናን በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ፣ ምክር እንዲያገኙ፣ የሌሎችን ጉድለት እንዲሞሉ፣ በህብረት እንዲጸልዩ እና የሕይወትን ውጣ ውረድ የሚጋፈጡበት አቅም ከወገኖች እንዲያገኙ ማድረግ፡፡

ክርስቶስ ካረገ በኋላ ያሉ ክርስቲያኖች ይሰበሰቡ የነበረው በቤት ውስጥ ነበር፡- ሐዋ 2፡24፤ 5፡42፤ 10፡ 22፤ 12፡12፤ ቆላ 4፡15፡፡

***ግጭት አፈታት*** | ግጭት ትክክለኛና እውነተኛ ከሆነ የሕይወት ክፍላችን አንዱ ነው፡፡ የዚህ አሳብ ግቡ ግጭትን ሙሉ በሙሉ መፍታት (በፍጹም የማይቻል ስለሆነ) አይደለም፡፡ ነገር ግን ጥርት ባለና ውጤታማ በሆነ ተግባቦት፤ ነገሩን በተቻለ መጠን ለይቶ በማውጣት በተረጋጋ መንፈስ መፍትሄ ላይ መድረስ ነው፡፡

ግጭት ሲከሰት፡-

- በጸሎት ወደ እግዚአብሔር መቅረብና በዚህ ግጭት አፈታት ውስጥ መንፈስ ቅዱስ እንዲመራችሁ ልመናችሁን አቅርቡ፡፡
- ሌሎችን ስሙ፤ በምትሰሙበት ወቅት ግን እነርሱ የተነሱበትን አሳብ መረዳታችሁን እርግጠኛ ሁኑ፡፡
- ሌሎች የሚያስቡትን እንደምታውቁ ራሳችሁን አታሳምኑ፡፡
- ለዚህ መነሻ የሆኑትን ጉዳዮች በመለየት እያንዳንዱ ጉዳይ የሚያመጣውን መዘዝ ተገንዘቡ
- አሸናፊ ተሸናፊ ድምጽ ከመሰብሰብ ይልቅ ስምምነት ላይ ለመድረስ(ምንም እንኳን የሁሉ ሰው ምርጫ ባይሆንም በአንድ ጉዳይ ላይ ተስማምቶ) መስራት፡፡

"እንደዚህ አስባችሁ ታውቃላችሁ፤ መቶ ፒያኖዎች በአንድ አይነት የቅኝት ማስተካከያ መሳሪያ ቢቃኙ በአንድ በመቃኘታቸው ብቻ አንዳቸው ከሌላቸው ጋር አንድ አይነት ቅኝት እንደሚኖራቸው ታውቃላችሁ? ሁሉም በአንድ ቅኝት የሚሆኑት አንዳቸው ሌላቸውን ተመልክተው አይደለም ነገር ግን በጣም በጥራት ስለተቃኙ ነው፡፡ በተመሳሳይ መቶ አማኞች ሕብረታቸውን በመጠበቅ ላይ ብቻ ትኩረት አድርጎ ከመንቀሳቀስ ይልቅ አይናቸውን በክርስቶስ ላይ ብቻ አድርገው ቢንቀሳቀሱ በበለጠ ወደሚያዳኝ ህብረት ይደርሳሉ፡፡" *-A.W. Tozer*

"ለብቻችሁ ልታከናውኑት የምትችሉት ብዙ ነገሮች ቢኖሩም...ክርስትናን መኖር ግን ከእነዚህ አንዱ አይደለም፤ በወንድሞች መካከል ያለ ፍቅር፤ ከእግዚአብሔር ፍቅር አይለይም፡፡" *-William Ham*

"የሚጠሉንን ለመውደድ አንድ መንገድ ብቻ ነው ያለው...የእነርሱን የከፋት አሳብ ረስተን፤ እነርሱን እንድንወድ የሚመራንን የእግዚአብሔርን መልክ በእነርሱ ውስጥ መመልከት" *-John Calvin (16th century Reformer)*

## 5. በኃይል የተሞላ አምለኮ እና ጸሎት

**ፍቺ/ትርጉም** ቤተክርስቲያን እንደ እግዚአብሔር ቤተሰብ ስትሰበሰብ ልትፈጽም የምትችለው አንድ ጉዳይ እግዚአብሔር አብን ማምለክ፣ በደላችንን መናዘዝ፣ አድናቆታችንን መግለፅ፤ ከዚህም በተጨማሪ ለጸሎት እና ለአገልግሎት ራስን መለየት ነው፡፡

*"በሐዋርያትም ትምህርትና በኅብረት እንጀራውንም በመቍረስ በየጸሎቱም ይተጉ ነበር። እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ በሕዝብ ሁሉ ፊት ሞገስ ነበራቸው።"* ሐዋ 2፡42፣47

**ይዘት እና ዘይቤን መግለጽ** | የአምልኮ አፈጻጸም መንገድ/ዘይቤ

የቤተክርስቲያን የአምልኮ አፈጻጸም ላይ ተጽዕኖ የሚፈጥሩ ብዙ መንስኤዎች አሉ፡፡ ከዚህ በታች ያለው የመገምገሚያ ቅጽ አምልኮ መሪዎች ያላቸውን አሳብ እንድታውቅ ይረዳሃል፡፡ በዚህ ጉዳይ ትክክለኛ ወይንም ትክክለኛ ያልሆነ መልስ የለም፡፡

የዚህ ቅጽ ዋና አላማ ለግምገማ እና እቅድ ውይይት ለመጀመር የሚያስችል አሳብን ማስገኘት ብቻ ነው፡፡ በዚህም ቤተክርስቲያኒቱ ምን አይነት የአምልኮ አፈጻጸም ስልት/ዘይቤ እንደምትከተል እና የትኛው ይቀጥል የትኛው ይስተካከል የሚለውን ነጥሎ በማውጣት ለግንዛቤ እንዲወስድ ይረዳል፡፡

**ግምገማ** | የሰርቶማሳያው ዘይቤ

| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
|---|---|---|---|---|
| አንደመጣልን | | የታቀደ | | በዝርዝር የቀረበ |
| ስሜታዊ | | ስሚታዊ | | ቁጥብ |
| ጥቂት | | አማራጭ ያለው | | ብዛት ያለው |
| ጥቂት | | ተሳታፊዎች | | ብዙ |
| ጥቂት | | ቴክኖሎጂ | | በቂ |
| ያላመነ | | ትኩረት | | አማኝ |
| ባህላዊ | | ቡዚቃ | | ዘመናዊ |
| በዕውቀት | | ስብከት | | ስሜታዊ |
| ጥቂት | | አገልጋዮችን ለአገልግሎት ስንጋብዝ | | ብዙ |
| ለሁሉ/በአደባባይ | | ምላሽ | | በግል |
| ለሁሉ ክፍት የሆነ | | ለጎብኚዎች | | ለጎብኚዎች ዝግ የሆነ |
| በአንድ ግልሰብ | | መሪነት | | በቡድን |
| ልብሰ ተክህኖ | | አለባበስ | | ማንኛውም አይነት |
| ክብረበዓል መሰል | | ድባብ | | በጨዋነት የተሞላ |

ከቤተክርስቲያኒቱ መሪዎች ጋር ቤተክርስቲያናችሁ ምን አይነት የአምለኮ ዘይቤ እንደምትከተል ተወያዩ፡፡ ዓላማው የእናንተን ተሳትፎ እውቅና መስጠት ነው፡፡ የአምልኮ ዘይቤን የሚወስኑ ብዙ ሁኔታዎች አሉ፡፡ በመገምገሚያ ቅጹ ላይ የተገለጡት ጥቂቶቹ ናቸው፤ እናንተ የቤተክርስቲያናችሁን ለዩ ባህሪ በማጥናት ሌሎች መስፈርቶችን መጨመር ትችላላችሁ፡፡ ይህ የመገምገሚያ ቅጽ የእንያንዳንዱን ተሳታፊ ምልከታ የሚለካና ስለአምለኮ አገልግሎት ለሚደረግ ውይይት በር ከፋች ነው፡፡ የህን ቅጽ ለመጠቀም ተመራጭ መንገድ ብለን እኛ የምንመከረው፤ ተሳታፊዎች ቅድሚያ በትንንሽ ቡድኖች በግል ቀድመው ይሙሉትና ከጠቅላላው ቡድን የሚሰበሰበውን አማካይ ወስዶ ስለውጤቱ በጋራ መወያየትን ነው፡፡ የግምገማ ጥያቄዎቹ ውይይቱን መል ለማስያዝ ይጠቅማሉ፡፡

*የቤተክርስቲያንህን ጤናማነት አረጋግጥ የሚለውን የመገምገሚያ ቅጽ እንዴት መጠቀም እንደሚቻል በማስተዋወቅ ወደፊት ሊጠቀሙበት እንደሚችሉ ማሳሰብ፡፡*

ምን አይነት የአምልኮ ዘይቤ ለእናንተ አውድ ተገቢ ይሆናል?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

ምን አይት ሙዚቃ፣ ቴከኖሎጂ እና የመሳሰሉት...ሰዎች እግዚአብሔርን እዲያከብሩ፣ ኃጢያታቸውን እዲናዘዙ፣ አምልኮአቸውን እንዲያቀርቡ እና ምልጃቸውን እንዲያሰሙ ይረዳሉ?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

**“አምልኮ ማለት...**

- ሁለንተናችንን ለእግዚአብሔር ማቅረብ፤
- ቅድስናውን መረዳት፤
- አሳባችንን ከእውነት ጋር ማኖር፤
- ተመስጦአችንን በእርሱ ውበት ማንጻት፤
- በሕይወታችን ለሚገለጠው የእርሱ ፈቃድ እና አላማ ታዛዥ መሆን፡፡

እነዚህ ሁሉ ወደ ውዳሴና በጣም ለአምልኮ ቅርብ ወደ ሆነ ስሜት ይለወጡ እና ወደራስ ተኮርነት ለሚመራን የውርስ ኃጢአት ፍቱን መድኃኒት ይሆናል፡፡” *-William Temple*

"ወንጌል ስርጭት የቤተክርስቲያን የመጨረሻ ጥሪ አይደለም፤ ሁሌም የወንጌል ስርጭትን ስፍራ አምልኮ ይወስደዋል፤ ምክንያቱም ወንጌል ስርጭት የሚኖረው አምልኮ በሌለበት ስፍራ ስለሆነ፡፡" *-John Piper*

**ማስታወሻ**

# ክፍለትምህርት አራት

# ቤተክርስቲያን ለመትከል ምን አይነት ደረጃዎችን አንከተል?

### ዓላማ

*Planting Healthy Churches* የተሰኘው መጽሐፍ በቤተክርስቲያን ተከላ ወቅት ልንከተላቸው ደረጃዎች በተመለከተ ልምድ ያላቸው ጸሐፊያንን ምክረአሳብ አቅርቦልናል፡፡ እኛም ከእነዚህ ቤተክርስቲያን ተከላ ደረጃዎች ውስጥ በብዙ የቤተክርስቲያን ተከላ ውስጥ አገልግሎት ላይ የዋሉትን ሞዴሎች አጠር አድርገን አቅርበናል፡፡ የዚህ ዓላማ ቤተክርስቲያን ተከላ ላይ የተሰማራው አገልጋይ ጤናማ ማህበረምዕመን ይኖረው ዘንድ ማድረግ የሚገባውን ሂደት በቅደም ተከተል ማስቀመጥ ነው፡፡

ይህን ክፍለትምህርት አንድን ጉዳይ ለመፈጸም ያለበቂ ዝግጅት ስለተነሳና ስላልተሳካለት አንድ ሰው በማንሳት ጀምር፡፡ ለምሳሌ፤ አንድ ሰው ወደ ሩቅ ሃገር ለመጓዝ አስቦ የተነሳ ነገር ግን ለጉዞው የሚሆን ውሃ እና ስንቅ ሳይዝ ጉዞ መጀመሩን መንገር፡፡ ምን የሚፈጠር ይመስላችኋል?

### ቤተክርስቲያን ከመትከላችን በፊት

እነዚህን የዝግጅት ዝርዝሮች እየሰማችሁ፤ እናንተ የተከላችሁትን ቤተክርስቲያን በምን አይነት ዝግጅት እንደተከላችሁ እና ምን አይነት ደረጃዎችን እዳለፋችሁ ማስታወሻችሁ ላይ አስፍሩ፡፡

### 1. *መንፈሳዊ ዝግጅት*

- ምሳሌ፡- የአንጾኪያ ቤተክርስቲያን (ሐዋ 13፡1-3)
- ጸሎት (በግል እና በህብረት)፣ ጾም ጸሎት፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት
- የምልጃ ቡድን (ጸሎት ጓድ) በቤተክርስቲያኒቱ ውስጥ ላለ ማንኛውም ጉዳይ የሚጸልዩ፡፡

---

---

### 2. *ሙያዊ ዝግጅት*

- እግዚአብሔር ለእንዲህ ያለ አገልግሎት እንደጠራን፤ በዚህም ቤተክርስቲያኒቱ እንደምትባረክ የሚሆን ማረጋገጫ፡፡
- ሌሎችን ወደአገልግሎቱ የመጋበዝ እና የማሳተፍ ብቃት
- በወንጌል ስርጭት፣ ስብከት፣ ማስተማር እና ማስተዳደር ዙሪያ ስልጠና መስጠት

---

---

### 3. የማህበረሰብ ስብጥር እና ብዛት ዝግጅት

- የማህበረሰቡን ባህሪይ ማወቅ

- በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን ግብአት እና ተግዳሮት መገንዘብ

______________________________________________________________

______________________________________________________________

## 4. ፍልስፍና ነክ ዝግጅት

- የቤተክርስቲያኒቱን ተከላ ግብን ጥርት አድርጎ ማቅረብ፡-
  - ቤተክርስቲያኒቱ በምትገኝበት ስፍራ ማህበረምዕመኗ እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያንነት ትታወቃለች
  - ቤተክርስቲያ ምን ልትሰራ ትችላለች (አምልኮ፣ ትምህርት፣ አገልግሎት፣ ወንጌል ስርጭትና ሌሎችም...)
  - እንዴት ነው ውሳኔዎች የሚወሰኑት፤ ተግዳሮቶችስ የሚቀረፉት
  - እንዴት ነው አገልግሎቱ ያልተቋረጠ የገንዘብ ፍሰት የሚኖረው

______________________________________________________________

______________________________________________________________

## 5. ስልታዊ ዝግጅት

- ምን አይነት የቤተክርስቲያን ሞዴል እደምትጠቀም ለይተህ እወቅ
- የሰዎችን ስጦታ፣ ሊደረሱ የታቀዱትን የማህበረሰብ ክፍሎች፣ ለስራ የሚያስፈልግ እና በእጅ ያለ ግብአትን ለይ

______________________________________________________________

______________________________________________________________

በዚህኛው ክፍል ደግሞ አሰልጣኙ ቤተክርስቲያን ለመትከል የሚወሰዱ እርምጃዎችን በቅደም ተከተል ካስተዋወቀ በኋላ ተሳታፊዎች ደግሞ እነዚህን መንገዶች በመጠቀም አዳዲስ የቤተክርስቲን ተከላ ዕቅዶችን እንዲያዘጋጁና እንዲወያዩ እድል ስጥ፡፡

## 6. የስሜት ዝግጅት

- ራስን የመግዛት ብቃት እና ጠንካራ ምርጫዎችን የመምረጥ አቅም
- ሂስ እና ግለሂስን መቀበል እና ከዚያ የመማር ብቃት
- ለቤተሰብ እና ለግል ጤናማ ሕይወት ትኩረት መስጠት

______________________________________________________________

______________________________________________________________

# አምስቱ ቤተክርስቲያን የመትከል ደረጃዎች




- የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋዩ ተምሳሌታዊ ማስረጃ | 1 ቆሮ 3፡6-9
- የገንቢው ተምሳሌታዊ ማስረጃ | 1ቆሮ 3፡10

1. **ወንጌል ስርጭት** | አዳዲስ ሰዎችን _መተዋወቅ_

የቤተክርስቲያንህ አባል የሚሆኑ ምዕመናን ከየት ነው የምታገኘው?

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

ሰዎችን በወንጌል ለመድረስ ምን አይነት ስልት ትጠቀማለህ?

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

2. **ደቀመዝሙርነት** | ትናንሽ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድን_ማደርጀት_
   እዴት ነው ወደጌታ የመጡ ሰዎችን ደቀመዝሙር የምታደርጋቸው?

______________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

3. **አባልነት** | ለቤተክርስቲያን የሚሆን መሰጠትን _አደርጅ_______
   ደቀመዛሙርትን ከምዕመናን ጋር የማዋሃዱ ሂደት ምን መሆን አለበት?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

   የአባልነት መስፈርት እና ኃላፊነት ምን መሆን አለበት?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

4. **መሪነት** | መሪነትን___መለየት__ እና ማሳደግ
   እንዴት ነው አዳዲስ መሪዎችን የምትለየው?

__________________________________________

__________________________________________

__________________________________________

አንዴት ነው አዳዲስ መሪዎችን የምታሰለጥነው?

__________________________________________

__________________________________________

__________________________________________

5. **የአምልኮ አገልግሎት**| የአምለኮ አገልግሎቱ እና የማበረሰብ አገልግሎቱን _____ጀምር__

በዚህ ክፍለትምህርት ስምንቱንም ሞዴሎች ለመተዋወቅ ጊዜ አይበቃም፡፡ በመሆኑም ከእነዚህ ሞዴሎች ውስጥ ላለህበት አውድ ቅርብ ናቸው የምትላቸውን ሶስቱን በማንሳት በጥልቀት ማብራራት እና ሌሎቹን እንደአማራጭ በጥቂቱ መዳሰስ ይቻላል፡፡ ይህን ማድረግ ካልተቻለ ደግሞ ጠቅላላውን ተሳታፊ ለስምንት በመክፈል ለእያንዳንዱ ቡድን አንድ ሞዴል በመስጠት ስምንቱም ቡድን ለጠቅላላው ተሳታፊ እንዲያቀርብ በማድረግ ሁሉንም ሞዴሎች መተዋወቅ ይቻላል፡፡ በ www.multiplicationnetwork.org ተብራርተው የተዘረዘሩ ሌሎች ሞዴሎችን ታገኛላቹ፡፡

እንዴት እና መቼ የቤተክርስቲያቱን የአምልኮ ጊዜ እንዲሆን የምትወስነው?

_______________________________________________________________________________

_______________________________________________________________________________

_______________________________________________________________________________

ምን አይነት የማበረሰብ አገልግሎትን ነው ቀድመህ የምታደራጀው?

_______________________________________________________________________________


_______________________________________________________________________________

_______________________________________________________________________________

## ስምንት በቤተክርስቲያን ተከላ ውስጥ የሚጠቅሙ ሞዴሎች

ቤተክርስቲያን ተከላን የተመለከቱ 22 ሞዴሎች ከመልካ ኢጋጣሚያቸው እና ከነስጋቶቻቸው እናገኛለን፡ ፡ ታዲያ በዚህ ክፍል በአብዛት ጥቅም ላይ የዋሉ ስምንት ሞዴሎችን እንመለከታለን፡፡


በማንም ላይ ያልተደገፈ ግንባር ቀደም አገልጋይ ሞዴል




በዚህ ሞዴል ቤተክርስቲያን ተከላው የተካሄደው ከዚህ ቀደም ወንጌል ሰምተው በማያውቁ ማህበረሰቦች ውስጥ ሲሆን፤ አገልጋዩ ከምንም አይነት ድርጅት (ለምሳሌ፡- እናት ቤተክርስቲያ ወይንም ሌላ የኃይማኖት ተቋም) ድጋፍ ሳያገኝ በፈቃዱ የሚሰራው ነው፡፡ እንዲህ ያው አገልጋይ አንድ ቦታ ቤተክርስቲያን ሲተከል እና ሲደላደል ወንጌል ሰምቶ ወደማያውቅ ሌላ ስፍራ ይንቀሳቀሳል፡፡

| ጥቅም | ጉዳት |
| --- | --- |
| ሀ. የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋዩ ግንባር ቀደም የመሆን መንፈስ በቀላሉ ወደሌሎች የሚጋባ ሲሆን የሚመራው ቡድንም ተግዳሮትን ለመቋቋም እንዲነቃቃ ያደርገዋል፡፡<br>ለ. ለቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋዩ የሚታዘዙ እና የእርሱን ጥልቅ የአገልግሎት ፍቅር እና መስዋዕትነት ለመካፈል የሚፈቅዱ ምዕመን ማግኘት<br>መ. ለመሪነት እና አገልግሎት ብዛት ያላቸውን እድሎች መፍጠር፡፡<br>ሰ. ግንባር ቀደም አገልጋዩ የፈለገውን በፈለገው ጊዜ የመወሰን ፍቃድ ያገኛል፤ ምክንያቱም ከእርሱ በላይ ሌላ ባለስልጣን ለዚያች አዲስ ቤተክርስቲያን ስለሌለ፡፡ | ሀ. ከአገልጋዩ የበላይ የሚባል ሰውና ተጠያቂነት ስለማይኖር የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋዩ ሊሰራ ካለው ስህተት ለመከልከል የሚረዳው ሰው ማጣት<br>ለ. ለረጅም ሰዓት ያለእረፍት በመስራት እና ምንም አይነት ድጋፍ ከሌሎች ባለማግኘት ከቤተሰብ ጋር ያለ ግንኙነት መላላት እና ችግር ውስጥ መግባት፡፡<br>መ. በተደጋጋሚ የሚከሰት የገንዘብ እጥረት<br>ሰ. በትዕቢት የተሞላ አሳብ እና እያዳንዱን አባል የመቆጣጠር  ፍላጎት፡፡<br>ረ. ምንም አይነት ድጋፍ አለማግኘት ወደ ተስፋማጣት ከፍ ሲልም የቤተክርስቲያን ተከላ አገልግሎቱን መተው፡፡ |


## 2. እናት እና ልጅ ሞዴል




ከሌሎች በተለየ በብዛት ጥቅም ላይ የዋለ የቤተክርስቲያ ተከላ ሞዴል ይህ ሁለተኛው ሞዴል ነው፡፡ “እናት” ቤተክርስቲያን ቤተሰቦችን እና መሪዎችን ብነወጌል ወዳልተደረሱ አዳዲስ ስፍራዎች ስትልክ ለመኖር የሚያስፈልጋቸውን ግብአት በሙሉ ታዘጋጃለች፤ ለዚህም ነው ይህ ሞዴል እጅግ ውጤታማ ሞዴል የሆነው፡፡

| ጥቅም | ጉዳት |
| --- | --- |
| ሀ. ቤተክርስቲያን ተከላ ውስጥ የሚሳተፉ፤ የአዲሲቱ ቤተክርስቲያን ጀማሪዎች ከእናት ቤተክርስቲያናቸው ጋር ተመሳሳይ የአገልግሎት ፍልስፍና ይኖራቸዋል፡፡<br>ለ. አዲሲቱ ቤተክርስቲያን ራሷንችላ እስከትቆም ድረስ ከእናት ቤተክርስቲያን በቂ የግብአት ድጋፍ ታገኛለች፡፡<br>መ. እናት ቤተክርስቲያን አዳዲስ መሪዎችን ለማብቃት ትገደዳለች<br>ሰ. እናት ቤተክርስቲያን የማያቋርጥ ድጋፍ እና ክትትል ለቤተክርስቲያ ተከላ አገልጋዩ ታደርጋለች<br>ረ. በአጭርጊዜ ውስጥ ብዙ ውጤት ማስመዝገብ ይችላሉ፤ ምክያቱም የእናት ቤተክርስቲያ ድጋፍ ስለማይለያቸው፡፡<br>ሸ. ቤተክርስቲያኚቱ እደተቋቋመች በማህበረሰቡ ዘንድ የታወቅች እና የተረጋጋች ትሆናለች፡፡ | ሀ. ብዙ አዳዲስ ቤተክርስቲያናተን መትከል፣ ዝግጅት እና መስዋዕትነትን ይጠይቃል፡፡<br>ለ. በእናት ቤተክርስቲያ ላይ ጥገኛ የመሆን አዝማማሚያ<br>መ. የተተከለችው ቤተክርስቲያ የእናት ቤተክርስቲያ ግልባጭ (a ‘clone’) በመሆን የራሷ የሆነ ልዩ መታወቂያ ባህሪ ያላት እዳትሆን ያደርጋል፡፡<br>ሰ. በእናት ቤተክርስቲያን ላይ የስሜት መረጋጋት ተግዳሮት ያስከትላል፤ ምክንያቱም በእናት ቤተክርስቲያኚቱ ውስጥ ያደጉ ምዕምናን ወደአዳዲስ አጥቢያዎች ስለመሄዱ፡፡ |

## 3. የቅኝ ገዢ ሞዴል





**እናት ቤተክርስቲያን** **ልጅ ቤተክርስቲያን**

ይህ ሞዴል እናት እና ልጅ ካነው ሞዴል ጋር በብዙ የሚስማማ ሲሆን፤ ለየት የሚያደርገው ቤተክርስቲያን ለመትከል የሚመለመለው ቡድን የራሳቸውን ወጪችለው፣ ስራ ፈልገው እና በዚያ ሩቅ በሆነ ስፍራ ራሳቸውን የሚያደራጁበት ሞዴል ነው፡፡

| ጥቅም | ጉዳት |
|---|---|
| ሀ. ቤተክርስቲያኝ ተከላ የተሰማራው ቡድን ለክርስቶስ እና ለታላቁ ተልዕኮ መስዋዕትነት ለመክፈል የተዘጋጁ ናቸው፡፡<br>ለ. የዚህ የቅኝ ገዢ ቡድን ለአዲሲቱ ቤተክርስቲያ ተከላ ቤታቸውንም ቢሆን ለመስጠት ወደኋላ አይሉም፡፡ | ሀ. ቤተክርስቲያኒቱ ስትጀመር በትንሽ የሰው ቁጥር መጀመሯ<br>ለ. ከእና ቤተክርስቲያን ያላቸው ርቀት በቂ ክትትል አዲሲቱ ቤተክርስቲያን እዳታገኝ  ያደርጋታል፡፡ |

## 4. ጥምር-ጉባኤ ሞዴል





በአንዳንድ ከተሞች ሁለት የተለያዩ ቋንቋ ተናጋሪዎች (ለምሳሌ፡- ሂሰፓኒክ እና እስያውያን) አንድን ህንጻ በጋራ ይጠቀማሉ፤ እነዚህ ቡድኖች የራሳቸው የሆነ መሪ እና መጋቢዎች ያላቸው ሲሆን ህንጻውን በማሳመር እና አንዳንድ ግብአቶችን በማሟላቱ ረገድ እኩል የሆነ የገንዘብ ድጋፍ ያደርጋሉ፡፡

| ጥቅም | ጉዳት |
|---|---|
| ሀ. ከገንዘብ ቁጠባ አንጻር ትርጉም የሚሰጥ የግብአት መጋራት ነው | ሀ. የቤተክርስቲያኒቱ ህንጻ በተደጋጋሚ አገልግሎት ስለሚሰጥ አንዱ ቡድን ከተወሰነለት የጊዜ ሰሌዳ ውጪ፤ ቤተክርስቲያቱ |

| | |
|---|---|
| ለ. የንብረት እና የግብአት ጥቅምን ከፍ ያደርጋል<br>መ. ከወንጌል ስርጭት አንጻር በጣም ሳቢ ነው<br>ሰ. በተለያዩ ቋንቋዎች እና የአምልኮ ዘይቤዎች ለመገልገል ምርጫ እንድናገኝ እድል ይሰጠናል፡፡<br>ረ. ዘረኝትን እና ማግለልን ለመስበር ወሳኝ ምዕራፍ ይሆናል፡፡ | አንድ ጊዜ ካሳወቀችው ፕሮግራሞች ውጪ አዳዲስ ፕሮግራሞችን ማድረግ አትችልም፡፡<br>ለ. የቤተክርስቲያኒቱ ምዕምናን ብዝሃነትን ለማስተናገድ የሚሆን ዝግጅት ከሌላቸው፣ ከዘረኝነት ጋር ተያይዞ የሚመጣኝ ተግዳሮት ለማለፍ አቅም ካላዳበሩ ለምሳሌ፡- ጥሩ የተግባቦት ዕውቀት እና ችሎታ ከሌላቸው፣ ሰውን ከንብረት በላይ ማክበር ካልቻሉ እንዲህ እና የመሳሰሉት ካሉ ሕንጻውን በጋራ በሚጠቀሙ ጎሳዎች መካከል ጥልን ሊፈጥር ይችላል፤ ይሁን እንጂ ይህን በቀላሉ ልናስወግደው የምንችለው ነው፡፡ |


## 5. ሳተላይት ሞዴል




ይህ ሞዴል ደግሞ በተወሰነ ጊዜ አንዴ የሚደረግ ስብሰባ ያቸው በከፊል ራሳቸውን በራሳቸው ሚያስተዳድሩ ብዙ ቤተክርስቲያናትን የያዘ ነው፡፡ እነዚህ ሳተላይት አጥቢያዎች ከእናት ቤተክርስቲያን ጋር ጥብቅ ግንኙነት ቢኖራቸውም፤ በዚያው ልክ ከፍ ያለ ራስን በራስ የማስተዳደር ነጻነት በሚገባ የተጎናጸፉ ናቸው፡፡

| ጥቅም | ጉዳት |
|---|---|
| ሀ. ትልልቅ ቤተክርስቲያናትን እና ትናንሽ የቤት ህብረትን ያጣምራል<br><br>ለ. ለስነመለኮት ተማሪዎች የወንጌል ስርጭት እና የማስተማር እድል እንዲያገኙ እድል ይፈጥራል፡፡<br><br>መ. እንዲህ ያሉ ቤተክርስቲያናት መባዛት፣ እድገት እና ሌሎች የመድረስ አቅም ከፍ ያለ ነው፡፡ | ሀ. እያዳንዱ አጥቢያ የራሱ የሆነ ግብአት እንዲኖረው ማስፈለጉ ከወጪ አንጻር ቀድሞ ሊታሰብበት የሚገባ መሆኑ<br><br>ለ. የእናት ቤተክርስቲያን እና የራስገዝ ቤተክርስቲያናቱ ሚና ሊደባለቅ መቻሉ፤ የአንዱ ኃላፊነት ከሌላው ጋር በሚጣረስበት ጊዜ ጥርት ያለና የማይረብሽ ሆኖ ቀድሞ በተዘጋጀ መመሪያ መሰረት አጥቢያ ቤተክርስቲያናቱ ከራስገዝነት ወደ በሙላት ራሱን ወደሚችል ቤተክርስቲያንነት ማደግ ያስፈልጋል፡፡ |


## 6. ሚሽነሪ ሞዴል




ሚሽነሪ ሞዴል በሰሜን አሜሪካ ወንጌላውያ አብያተክርስቲያናት ዘንድ ታዋቂ የሆነ ሞዴል ነው፡፡ ሚሽነሪው ፓስተር ከዚህ ብዙ ቤተክርስቲያናት ተባብረው ባቆሙት የሚሽነሪ ማዕከል በሚያገኘው ድጋፍ አማካይነት አዲስ ቤተክርስቲያ ይተክላል፡፡ ልክ ቤተክርስቲያኒቱ በአስተምህሮ፣ መሪነት እና በገንዘብ ራሷን የምትችለበት አቅም ላይ ስትደርስ አገልሲጋዩ መልቀቂያውን እስገብቶና ሌላ መሪን በስፍራው ሹሞ ያንን ቤተክርስቲያ ይለቃል፡፡

| ጥቅም | ጉዳት |
|---|---|
| ሀ. ይህ ሞዴል በአቅኚው/ግንባር ቀደም በሆነው አገልጋይ ሞዴል ውስጥ በሚገባ ይሰራል<br><br>ለ. ሚሽነሪ ሆኖ የተላከው ፓስተር በቂ ልምድ ያዳብራል፡ ፡<br><br>መ. ሚሽነሪው እና ቤተሰቡ በቂ የሆነ የገንዘብ ድጋፍ ይኖረዋል፡፡<br>ሰ. የሚደረግላቸው ኢኮኖሚያዊ ድጋፍ በአጭር ጊዜ ውስጥ የጸሎት ቤት እንዲገነቡ ይረዳቸዋል፡፡ | ሀ. የቤተክርስቲያ ተከላ አገልግሎት ድጋፍ በሚያደርገው የሚሽነሪ ድርጅት ወይንም አብያተክርስቲያናት ለድርጅቱ በሚያደርጉት ድጋፍ ላይ በከፍተኛ ሁኔታ ጥገኛ መሆን፡፡<br><br>ለ. ሚሽነሪ ፓስተሩ ተጨማሪ በጀት ለማፈላለግ እና እየሰራ ያለውን ስራ አፈጻጸም ለማስረዳት ወይንም ሪፖርት ለማድረግ በየጊዜው አገልግሎቱን ትቶ ለመሄድ ይገደዳል፡፡<br><br>መ. ባንዳንድ ሁኔታዎች የምትተከለው አዲስ ቤተክርስቲያን ራስዋን በገንዘብ እና ግብአት ከመቻል ይልቅ በሚሽነሪ ድርጅቱ ላይ ጥገኛ መሆን፡፡<br>ሰ. ብዙ ጊዜ ከሚሽነሪ ፓስተር በዚያ ስፍራ ከሚኖሩት መካከል ወደ ተሾመ ቋሚ ፓስተር የተሳካ ሽግግር ማድረግ አለመቻል፡፡ |


## 7. ቤተእመነታዊ ሞዴል



ይህ ህብረት የመመስረት አይነት ሞዴል ነው፡፡ እንዲህ ያው ሞዴል እውን የሚሆነው ብዙ ቤተክርስቲያናት ያለቸውን አቅም አሰባስበው እና ልምዳቸውን በመጠቀም ጥናት ላመድረግ፣ አካባቢዎችን ለመምረጥና የቤተክርስቲያን ተከላ ግብ ለማስቀመጥ ቃልኪዳን ሲያቆሙ ነው፡፡

| ጥቅም | ጉዳት |
| --- | --- |
| ሀ. ገንዘብን የተመለከተ ችግር ስለማይኖር በገንዘብ ጉዳይ ሁሉም ይህን ኃላፊነት ይጋራሉ፡፡<br>ለ. ውጤታማ የሆነ አስተዳደር ይኖራል፡፡<br>መ. በዛ ያለ አሳብ እና ሰው ለማግኘት በጥሩ ሁኔታ የተሰናሰለ/ የተያያዘ አደረጃጀት ይኖረዋል፡፡ | ሀ. በአጥቢያ ደረጃ ያለን የስራ መነሳሳትን እና ተሳትፎን ለመፍጠር ያለው ስፍራ በጣም ጥቂት ይሆናል፡፡<br>ለ. ቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋዩ በቤተእምነቱ በያዘው መሰረት ላይ ብቻ ጥገኛ እደሆነ እንዲሰማው ያደርጋል፡፡<br>መ. አገልጋዮቹ የሌሎች አካባቢዎችን ፍላጎት ማየት ከተሳናቸው "ነጠኝነትን" ያስፋፋል፡፡ |

## 8. ቅንጣት/ ትናንሽ የጥናት ቡድን ተኮር ሞዴል




ይህ ሞዴል የቤት ህብረትን እና ትናንሽ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖችን ምህዋር አድርጎ በመንቀሳቀስ ቤተክርስቲያኒቱን ስራ ለመስራት እና ለማደራጀት የሚጠቅም ነው፡፡ ሁሌም ግብ አድርጎ የሚንቀሳቀሰው የቤተህብረት መመስረትን እና ማብሳትን ሲሆን ከዚህ ጋር በተያያዘ መሪዎችንም የማብዛት እና የማብቃት ስራ ለመከወን ይረዳል፡፡

| ጥቅም | ጉዳት |
| --- | --- |
| ሀ. መሪዎችን ማፍራን እና ማብቃትን ያሳልጣል<br>ለ. ላዳኑ ሰዎች የሚመች ሁኔታን ይፈጥራል<br>መ. ቀጥተኛ የሆነ ተሳትፎ እንዲኖር በበለጠ እድል ይከፍታል | ሀ. የቤተክርስቲያኒቱ መሪዎች ተራማጅ የሆነ አመራር ስልት ከሌላቸው የቤተክርስቲያኒቱ ሕልውና ሊያከትም ወይንም ያለምንም እድገት ባለችበት ልትቆም ትችላለች፡፡<br>ለ. ይህን ሞዴል ለማዳበር ከፍ ያለ ቁጥር ያቸው መሪዎች ያስፈልጋሉ<br>መ. በትናሽ ቡድን የታቀፉ ሰዎች አንዳቸው ከሌላቸው ጋር ያላቸው መስተጋብር ጠንካራ ስለሚሆን፤ በዚህ ምክንያት ሰዎች ምቾታቸውን ለመጠበቅ ሲሉ አዳዲስ ቤተክርስቲያናት ይተከሉ ዘንድ ኃላፊነት ወስደው ቡድናቸውን መተው አይፈልጉም፡፡ |

**ሃሳባችሁን ግለጹ፡-**

- የትኛውን የቤተክርስቲያ ተከላ ሞዴል በበለጠ ታውቁታላችሁ?
- አሁን ያላችሁበት ቤተክርስቲያን የትኛውን ሞዴል ትከተላላች ወይንም ወደፊት የቱን ሞዴል ብትከተል ይሻላል?
- የመረጣችሁትን ሞዴል ጠቀሜታ እንዲጨምር ምን ልጣደርጉ ትችላላችሁ?
- እዴት ነው የመረጣችሁት ሞዴል የሚያስተከትለውን ጉዳት መቀነስ ወይንም ማካካስ? የምትችሉት?

# ሰርቶማሳያ መርሃግብሩን ማጠቃለል

# ሶስት መሰረታዎ ግብአቶች፡-

## ተጠያቂነት

በብዙ ቦታዎች ለማስረዳት እንደተሞከረው የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋዩ ውጤታማ የሚሆን በየተወሰነ የጊዜ ርቀት ስለሰራው ስራ ቀላል እና ግልጽ በሆነ መልኩ ሪፖርት ማድረግ እንደላበት ሲያውቅ ነው፡፡ ሪፖርቱም የሚቀርበው አብሮት ለሚሰራ ቡድን፣ ክትትል እና ድጋፍ ለሚያደርግለት አገልጋይ፣ ወይንም የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋዩን ለሚደግፈው አማካሪ ነው፡፡

## ድጋፍ እና ክትትል የሚያደርግ አገልጋይ

የቤተክርስቲኝ ተከላ አገልጋዩ ስለእርሱ ሕይወት እና ስራ የሚጨነቅ፣ የሚያበረታታ እና መንፈሳዊ ድጋፍ የሚሰጥ ግለሰብ ካለው ውጤታማ የመሆን እድሉ ከፍ ይላል፡፡ አገልጋዩ የሚጎበኝበት ድግግሞሽ የተለያየ ቢሆንም በወር ውስጥ ቢያኝስ አንድ ጊዜ ሊጎበኝ ይገባዋል፡፡

## ተጨማሪ ወይንም የመዋቅር ድጋፍ

ጥናቶች እንደሚያመለክቱት እውቅና የተሰጣቸው፣ እንክብካቤ የሚደረግላቸው እና ትልቅ መዋቅር ወይንም ተጨማሪ ድጋፍ የሚደረግላቸው ብቻቸውን ከሚሰሩ ይልቅ ተጠቃሚ ናቸው፡፡ ይህ ድጋፍ ኢኮኖሚያዊ ድጋፍን የማይመለከት ቢሆንም፤ በአንዳድ ሁኔታዎች እዲህ ያውን ድጋፍ ሊያጠቃልል ይችላል፡፡

**የመገምገሚያ ቅጽ**

1. ይህን አጥቢያ ማብዛት መተዋወቅ ሰርቶማሳያ እዴት ትገመግመዋለህ?

   ☐ አጅግ በጣም ጥሩ ☐ በጣም ጥሩ ☐ ጥሩ ☐ መካከለኛ ☐ ደካማ

2. ሌሎች ይህን ሰርቶማሳያ እንዲሰለጥኑ ጥመክራለህ

   ☐ አዎን ☐ ምናልባት ☐ አይመስለኝም ☐ በፍጹም አልመክርም

3. በዚህ ሰርቶማሳያ ላይ ምን ልትጨምርበት ትችላለህ

   ________________________________________

   ________________________________________

   ________________________________________

4. ከዚህ ሰርቶማሳያ ምን ቢቀነስ ትመርጣለህ

   ________________________________________

   ________________________________________

   ________________________________________

5. ሰርቶማሳያውን የሚመሩትን አገልጋዮች ዝግጅት እዴት ትገመግመዋለህ

   ☐ አጅግ በጣም ጥሩ ☐ በጣም ጥሩ ☐ ጥሩ ☐ መካከለኛ ☐ ደካማ

6. ይህን ክፍለትምህርት በተመለከተ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተቀመጡት ስዕላዊ መግለጫዎች የትምህርቱን ጭብጥ ለማወቅ የሚያግዙ ናቸው

   ☐ በጣም የሚያግዙ ናቸው ☐ በመጠኑ የሚያግዙ ናቸው ☐ ይህን ያህል የሚያግዙ አይደሉም ☐ አያግዙም

7. ይህን ክፍለትምርት በተመለከተ ከአንተ አስተያየት ጋር የሚስማማውን አክብብ፡-

| | ከፍተኛ | | | | ዝቅተኛ |
|---|---|---|---|---|---|
| ክፍለ ትምህርት 1 ለምን ጤናማ ቤ/ክ እተክላለን | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| ክፍለ ትምህርት 2 ማነው ቤተክርስቲያን መትከል ያለበት | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| ክፍለ ትምህርት 3 እኛ ልንተክለው የምፈልገው ቤ/ክ ምን መምሰል አለበት | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| ክፍለ ትምህርት 4 ቤ/ክ ለመትከል ምን አይነት እርምጃ መውሰድ አለብን | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |

**8. ተጨማሪ አስተያየት ወይንም ጥቆማ፡-**

________________________________________

________________________________________

________________________________________

**ማስታወሻ**

________________________________________

________________________________________

________________________________________

multiplication network

*more churches, stronger churches*

## *የዕውቅና የምስክር ወረቀት*

# አጥቢያን የማስፋት መርህ

በተሰኘ ሰርቶ ማሳያ ስልጠና አጥጋቢ በሆነ ሁኔታ ተሳትፈው ስላጠናቀቁ
ይህ የዕውቅና የምስክር ወረቀት ተሰጥቷቸዋል

ይህ ስልጠና በ______________________________ቤ/ክ/ ድርጅት ትብብር የተዘጋጀ ነው

የተሳታፊው ስም__________________________________________________

ቦታ_________________________________ ቀን____________________

*ለቤተክርስቲያን እድገት እና ለአዳዲስ ቤተክርስቲያናት ተከላ አገልግሎት የታለመ የመሪዎች ስልጠና*

**WWW.multiplicationnetwork.org**